# የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት

ከጳውሎስ ኞኞ

መስከረም 1980
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| ርእስ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 7 |
| የ1928 ዓ.ም. ጦርነት የጠቡ መነሻ | 9 |
| የወልወል ግጭት | 12 |
| አፈወርቅ | 21 |
| በሊግ ኦፍ ኔሽንስ የተደረገ ክርክር | 29 |
| የኢጣሊያ ጦርነት ዝግጅት | 34 |
| ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ | 52 |
| የኢትዮጵያ ጦር | 55 |
| አጺ ሰለባ | 66 |
| መላኩ በያን | 68 |
| አድዋ | 70 |
| መቀሌ | 71 |
| ተምቤን | 87 |
| አምባአራዶም | 99 |
| ሽሬ | 108 |
| ማይጨው | 115 |
| የአሸንጌው እልቂት | 121 |
| ቦረና ነገሌ | 127 |
| የሐረር መያዝ | 136 |
| ጓንጉል ኮላሴ | 142 |
| የአዲስ አበባ መያዝ | 146 |
| ፲፱፻፳፰ | 150 |
| አቡነ ጴጥሮስ | 156 |
| የካቲት 12 ቀን | 158 |
| አብርሃም ደቦጭ | 171 |
| የባቡር አደጋ | 173 |

፲፱፻፷፱ .......... 178

የዘር ልዩነት .......... 186

ዘርአይ ደረስ .......... 191

፲፱፻፸ .......... 192

፲፱፻፸፩—፲፱፻፸፪ .......... 202

የአዲስ አበባ እንደገና መያዝ .......... 207

የጦርነቱ ፍጻሜ .......... 222

ዋቢ መጻሕፍት . .......... 226

## የተሳቤ ከአውሎስ ኛኛ፣

## ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች ።

በ1928 ኢጣሊያ ኢትዮጵያን እንዴት አሸነፈች? በአይሮፕላንና በመርዝ ጋዝ የሚለው መልስ የተለመደ ነው ። ብዙ ጊዜም ይህን በመስማቴ ምን ያህል ቦምብና መርዝ እንደተጣለ ለመግለጽ አስብ ነበር ። ጊዜው ሲደርስ ጥርትምቅሙን አጠረቃቅሜ በሙሉ ታሪኩን ሳይሆን በመጠኑ አቀረብኩት ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ካገራችን የታሪክ መጻሕፍት አልጠቀስኩም ። ያልጠቀስኩበትም ሁለት ምክንያቶች አሉኝ ። 1ኛ፤የኛ ታሪክ ፀሐፊዎች ለኛው ብቻ ስለሚያዳሉና ስለሚመሰክሩ ድር በድር እየሆነ ለማመን ስለሚያስቸግር ወጣቱ ትውልድ ናቅ ስለሚያደርገው ነው ። ወጣት አይደለሁም እንጂ እኔም ብሆን እንዲሁ ነኝ ። አንድ ያገራችን ተራኪ ሲተርኩ አንዱ ሰው 12,000 የኢጣሊያ ወታደር ማረከ ብለው ጽፈዋል ። ይህ ፈጽሞ የማይሆንም የማይቻልም ነገር በመሆኑ ታሪክን ማበላሸት ነው ። 2ኛው ምክንያቴ ፤ እኛው ለኛው ከምንመሰክርና እርስ በራሳችን ከምንሞካሽ ጠላት የሚመሰክረው ምስክርነት እንደ ቃል አጥጋቢ ስለምትሆን ብዙው የተሰበሰበው ከኢጣሊያውያን መጻሕፍት ነው ። ይህም የጊዜውን ጠላት ምስክርነት ያላወቁ ኢትዮጵያውያን ሲያውቁት ደስታም ፤ ኩራትም ይሰማቸዋል ብዬ ነው ።

በዚች መጽሐፍ ውስጥ አንዳንዱን ሰው አንዴ አንቱ ፣ አንዴ አንተ እያልኩ ጽፌአለሁ ። ይህ የሆነው 'ለምን አንቱ አልከው?' የሚል ጥያቄ ቢመጣብኝስ እልና 'ለምን አንተ አልከው? ነውር ነው' የሚል ቢነሳስ እያልኩ ለሁለቱም ወገኖች በማለት በሁለቱም ተጠቀምኩ ። አንዳንድ ቦታ ላይ ደግሞ የቀን ስህተት ሊያጋጥም ይችላል ። ይህም ከየመጽሐፍቱ ስለቅም እንዳገኘሁት ነው እንጂ የኔ አይደለም ። እኔ ለራሴ ጦርነት ቦታ ውዬም አላውቅም ።

በአተረጓጐሜ በተቻለኝ መጠን ለሁሉ ሰው እንዲገባ በማለት በቀላል ቃላትና በሚስማማ አረፍተ ነገር ያስማማሁት መስሎኛል ።

የቦታ ስሞች የማውቃቸውን ሳውቃቸው ፤ የማላውቃቸውን እየዞርኩ ማጣራት ነበረብኝ ። ይህን ለማድረግ ስላልቻልኩ በቀጥታ ከየመጽሐፉ ያገኘሁትን ስም ያስገባሁበት ቦታ አለ ። ባይበዛም መቼም ስህተት መሆኑ አይቀርምና በየቤታችሁ እዚያው እርሙት ።

ከሐተታው ይልቅ ፎቶግራፎችን አብዝቻለሁ ። ያውም አስቀርቼለት ነው ። ፎቶግራፎች ያበዛሁበት ዋናው ምክንያት አንድ ፎቶግራፍ ከሺህ ቃላት የበለጠ በቀላሉ ስለሚያስረዳ ነው ። ስለዚህ በሐተታና በንባብ ከማድከም በማለት ከሐተታው ቀንሼ ከፎቶግራፎቹ አብዝቻለሁ ።

አሳቤ ወይም አቀራረቤ ለታሪክ ተራኪነት ተነስቼ መራቀቄ አይደለም ። ኢጣሊያ የአርባ ዓመት የአድዋ ቂሙን አስታውሶ ሲነሳ እኛ ግን እውነተኛውን ታሪክ ሳናወራ 50 ዓመት ስላለፈው ለአንዳንዶች አንባቢያን እውነተኛውን ታሪክ ላላገኙ ኢትዮጵያውያን እንዲህ ነበር እያልኩ ያገኘሁትን ለማካፈልና ለማጫወት ያህል ነው ።

እስካሁን በተጻፉት ያገራችን የታሪክ መጻሕፍት በአብዛኛዎቹ እኔ እንዳነበብኩት የጦር መሪ የነበረ መኳንንትና መሳፍንት ሁሉ ጀግና እየሆነ ተጽፎአታል ።

ከውጭ አገር ታሪክ ፀሐፊዎች መጽሐፍት ያገኙሁት ግን ስለጦር መሪዎቻችን ብዙ ብዙ ብዙ ያወራል ።

ባገራችን የተፃፉ የታሪክ መጻሕፍት አንዳንዶቹን እንዳነበብኳቸው የንጉሡ ወዳጆችና ሥልጣን የነበራቸው ሰዎች ጀግኖች እየሆኑ ተሞግሰውበታል ። እኔ ግን ያገኘሁት የተገዳቢጦሹን ነው ። በዚች በቁንጽል ጽሑፌም ትውልዶቻቸው ባይቀየሙኝ ደስ ይለኛል ። ሌላውም ደግሞ ለምን ቀነስክ ብሎ ባይቆጣኝ እወዳለሁ ። ለራሴ የራሴ ምክንያት ስላለኝ ነው ።

ሌላው ነገር ፤ ባለፈው የታሪካችን ጽሑፍ ጀግኖች እንደፈሪ ተሰድበዋል ። አሞካሽተህ ወይም አበላሽተህ ጻፍ የሚል ትእዛዝ እንዳለባቸውም አውቃለሁ ። ቢሆንም እንደ አፈወርቅ ዓይነቱ ፤ እንደስለባ ዓይነቱ እንዴት ይረሳል? ከንጉሡ የተቀያየመ ፈሪ ፤ የስገዶ ጀግና መሆን የለበትም ። እንዲህ ከሆነ ሲቀር ሁሉም ቀሪ ነውና ትውልድ እውነቱን ያወጣዋል ።

ደህና እንሁን ።

# መ ግ ቢ ያ

ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ለሁለት ሺ ዓመታት ያህል የተደጋገመ ሙከራ ተደርጓል ፡፡ ኢትዮጵያውያን ግን አገራቸውን በሌላ ባዕድ ሳያሲዙ ባላቸው ኃይል ሲከላከሉ ቆይተዋል ፡፡ በኤሮፓም ሆነ በእስያ ወይም በአፍሪካ የሚገኙ ታላላቅ መንግሥታት ጉልበት እያገኙ ግዛታቸውን በሚያሰፋበት ጊዜ ኢትዮጵያንም ለመደ ረብ ብዙ ጊዜ ሞክረዋል ፡፡ ኢትዮጵያውያን ግን ለማንም ሳይበገሩና ሳይገብሩ እስካ ሁን አገራችንን አስከብረው ቆይተዋል ፡፡

መለስ ብለን ከታሪካችን ውስጥ በመጠኑ ብንመለከት የሚያኮራንንና የሚያስ መኩንን ታሪክ ማግኘት እንችላለን ፡፡ ከክርስቶስ በፊት በ336 በግሪክ ላይ ነግሶ የነበረው ታላቁ አሌክሳንደር ግዛቱን እያሰፋ ከመቄዶንያ ፣ ግብጽ ድረስ ተሻገረ ፡፡ ብዙ አገሮችም በጦር ሳይሆን ገና በዝናው እየፈሩ ገበሩለት ፡፡ ኩዊንቱስ ኩርቲውስ የተባለው የዘመኑ ታሪክ ፀሐፊ የአሌክሳንደርን ግዛት ማስፋፋትና ለጦርነት መነሳት ሲገልጽ "...ወጣቱ ንጉሥ ለጦርነት ሲነሳ የምወረው ግብጽን ብቻ አይደለም ፡፡ ኢት ዮጵያንም ጭምር ነው ፡፡..." ማለቱን ጽፏል ፡፡ አሌክሳንደር ዝቶ እንደተነሳው ከግብጽ ጀምሮ እስከ ህንድ ድረስ አስገበረ ፡፡ በመሀል ግን ኢትዮጵያ ከገባሪዎች ተነጥላ ቀረች ፡፡ አሌክሳንደር ስለ ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ሰምቶ ነበርና ከኢትዮጵያውያን ጋር ጦርነት ለመግጠም ፈራ ፡፡ ስለኢትዮጵያውያን የሚነገረው ጀግንነትም እውነት ለማረጋገጥ ሊመሰለው ራሱ አሌክሳንደር ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ለመሰለል ተነሳ ፡፡ ክሮኒክልስ ኦፍ ጆን ፤ ቢሾፕ ኦፍ ኒኩ በሚባለው መጽሐፍ ላይ እንደሚተርከው "አሌክሳንደር ከምርጥ የጦር አለቆቹ ጋር ሆኖ ሁሉም ተራ ሰው መስለው ለመሰለል ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ፡፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ህንደኬም አሌክሳንደር ተራ ሰው መስሎ ወደ ኢትዮጵያ ለመሰለል መግባቱን ሰማች ፡፡ ንግሥቲቱ እነኚያን እንግዳ ተራ ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥትዋ አስጠርታ እንዲህ አለች ፡፡ 'ዓለምን አንቀጥቅጠህ የገዛህ ታላቁ እስክንድር ሆይ ፤ ዛሬ በሴት እጅ ተይዘሃል' ስትለው ንጉሡ በመታወቁ ደንግጦ ጥበቧን አደነቀ ፡፡ የኢትዮጵያን ወታደር ብዛትና የሰላዮቿን ጥበብ አድንቆ 'ንግሥት ሆይ ፤ የተነገረኝ ሁሉ እውነት ነው ፡፡ ይህ በጦር የማይፈታ ሕዝብ ነውና እኔና አንቺ ተጋብተን ዓለምን እንግዛ' አላት" ይላል ፡፡

ኢትዮጵያን ለማስገበር ከተነሱት ታላላቅ የኤሮፓ ነገሥታት መሀል አንዱ አውጉስቶስ ቄሳር ነው ፡፡ የሮማው አግውስቶስ ቄሣር ኤሮፓንና አፍሪካን ፤ ኤስያንም ጭምር አስገብሮ በሥልጣኑ ሥር ካደረገ በኋላ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ29 ዓመት ላይ አይሎስ ጋሎስ በሚባል ጦር አዛዥ የሚመራ 10,000 እግረኛና 8,000 ፈረሰኛ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ላከ ፡፡ በዚያን ዘመን የአክሱም መንግሥት ገናና ስለነበር ፤ የኢትዮጵያ የባህር ኃይል ፈጽሞ የማይበገር መሆኑን ያወቀው አይሎስ ጋሎስ ጦሩን በግብጽና በዛሬው ሱዳን በኩል አሻግሮ የአክሱምን መንግ ሥት ለመውጋት ገሠገሠ ፡፡ ይህን የሰሙ ኢትዮጵያውያን ጦራቸውን ከትተው የአው ግስቶስ ቄሣርን ጦር ከወሰናቸው ማዶ አቆሙት ፡፡ ለብዙ ዓመታት ውጊያው ተካሂዶ ኢትዮጵያውያን አልበገር በማለታቸውና ከሮማ የመጣው ጦርም እየመነመነ በመሄዱ የሮማው ጦር አዛዥ አይሎስ ጋሎስ ከሮማው ንጉሥ በታዘዘው መሠረት ጦርነቱ በእርቅ አልቆ የተረፈው የሮማ ጦር ወደ አገሩ ተመለሰ ፡፡

በቅርቡ የአድዋን ጦርነት ብድር ለመመለስ ፋሺስቶች በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት እንዳወጁት ሁሉ በአውግስቶስ ቄሣር የደረሰውን ሽንፈት ብድር ለመመለስ በ54

ሟም በሮማ የነገሰው ኔሮ ፎክሮ ተነሳ ። የኔሮ አማካሪዎችም ፣ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን የማያስነኩና በጦርነትም የማይሸነፉ ሕዝቦች መሆናቸውን ነግረው ያሁኑ ወደ ኢትዮጵያ ጦር መላክ የባሰ ውርደት ይሆናል በማለት አስጠነቀቁት ።

ኔሮ የአማካሪዎቹን ምክር ቢሰማም የዘመኑን የኢትዮጵያን ጦር የሚሰልል የስለላ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ላከ ። እዚህ ላይ ሮማዊው የዘመኑ ታሪክ ፀሐፊ ሴኔካ ከፃፈው ታሪክ በጥቂቱ እንጥቀስ ። "ኔሮ የአባቶቹን ምኞት ለመፈፀም የአባይን ምንጭ የሚፈልጉ ናቸው ብሎ ለኢትዮጵያው ንጉሥ ደብዳቤ ጽፎ ሰላዮቹን ወደ ኢትዮጵያ ላከን ። የተላክነው ሰላዮች ኢትዮጵያ ውስጥ ክርመን ስንመለስ ሕዝቡ ጦረኛ መሆኑንና በአሁኑ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ጦር መላክ እንደማያዋጣ ነገርነው ። አገሪቱ ግን እጅግ በጣም ለም ናት አልነው" ሲል ከስለላ ቡድኑ ጋር አብሮ የነበረው ሴኔካ ጽፏል ።

ይህ ሁሉ ቢሆንም ኔሮ አባቶቹ ያልቻሉትን ኢትዮጵያን የማስገበር ምኞት እሱ እንደሚችል ተማምኖ ካምቢይስ በሚባል ጦር መሪ የሚመራ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ልኮ ጦሩ ድል ሆኖ መመለሱን ታሪክ ፀሐፊዎቹ ዲዩ ካሲዮ እና ፕሊኒ ጽፈዋል ።

ዛሬ በዓለም ላይ አሉ እንደሚባሉት አራቱ ኃያላን መንግሥታት ሁሉ ፤ ኢትዮጵያም በሶስተኛው መቶ ዓመት በዓለም ላይ አሉ ከሚባሉት አራቱ ኃያላን መንግሥታት አንዷ ነበረች ። ሂስቶሪካ አውጉስታ በሚባለው የታሪክ መጽሐፉ ማኒ በ275 ዓም እንደፃፈው "....በዓለም ካሉት አራቱ ታላላቅ መንግሥታት አንዷ ኢትዮጵያ ናት ። የኢትዮጵያው የአክሱም መንግሥት በወታደርና በጦር መሣሪያ የበለፀገ በመሆኑ ለወዳጅ አገሮች ርዳታ በመስጠት የታወቀ ነው...." ብሏል ። እነ ኮንቲሮስኒም ይህን አረጋግጠዋል ።

ኢትዮጵያን አስገብሮ ለመያዝ የተደጋገመ የውጭ ጦር ቢመጣም ኢትዮጵያውያን ባላቸው ኃይል የማይበገሩ ሆነው የሚመጣውን የውጭ ጦር ሁሉ መልሰዋል። ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን የማይለቁና የሌላ አገር የማይፈልጉ በመሆናቸው እንጂ እንደ ታሪክ ፀሐፊዎች መስካሪነት ከሆነ ኤሮፕንም ሆነ እስያን እያለፉ የሚይዙበት ብዙ ዘመን ነበር ። በ1298 የባህር ላይ ጉዞውን የጀመረው ማርኮ ፖሎ በፃፈው ታሪክ ስለኢትዮጵያውያን ሲገልጽ እንዲህ ይላል ። "...ሊታወቁት የሚገባ ነገር አለ ። በአበሻ ምድር ምርጥ የሆኑ ወታደሮች አሉ ። አብዛኞዎቹ ወታደሮችም ፈረሰኞች ናቸው ። ፈረስም በብዛት አላቸው ። በዚህም ምክንያት ተዋጊዎችና ኃይለኞች ናቸው ። በህንድ አገር ስላሉትና ከምናደንቃቸው አውቅ የሕንድ ወታደሮችም የሚበልጡ ናቸው ። ...." ብሏል ። ባጭሩ በዚሁ ይብቃን ።

———o———

# የ1928 ዓም ጦርነት

## የጠቡ መነሻ

እጼ ምኒሊክ ሲሞቱ የልጅ ልጃቸው ኢያሱ መንግሥቱን እንዲመሩ ተናዘዙ ። ልጅ ኢያሱ መንግሥቱን በሞግዚትነት ይዘው ማስተዳደር ጀመሩ ። ልጅ ኢያሱ መንግሥቱን በያዙበት ጊዜ አንደኛው የዓለም ጦርነት በመንቀሳቀስ ላይ ስለነበረ ልጅ ኢያሱ ከስላሙ በጥባጮች ከጀርመንና ከቱርክ ጋር ተዋዋሉ ። የነዚሀ የጦር ጎዶች ተቃራኒ የሆኑት ፈረንሣይ ፤ እንግሊዝና ኢጣሊያ ፤ ኢያሱን ለመጣል ቢሉ ተፈሪን አቀፉ ። በገንዘብም ሆነ በስብከት የአሮፓ ኃያላን ኢያሱን አስጥለው ዘውዲቱን ንግሥት ፤ ተፈሪን አልጋወራሽ አስደረጉ ።

ይሀ ከመሆኑም በፊት እንግሊዝና ኢጣሊያ "በኢትዮጵያ ውስጥ ያለንን ጥቅም ለማስከበር" በሚል ርእስ እ ኤ አ በ1891 ዓም በመጋቢትና በሚያዝያ ወር ውል ተፈራርመዋል ። እንደገናም ከሶስት ዓመት በኋላ እ ኤ አ በግንቦት ወር በ1894 ዓም "እንግሊሎ ኢታሊያ አግሪሜንት" በሚል ርእስ በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ያንሱን ጥቅም እንዲ ላይነካ የወዳጅነት ውል ተፈራረሙ ።

•የእነኚሀ የሁለቱ ኃያላን የጥቅም ማስከበር አንደኛዋን ባለጥቅምና ኃያል የሆነችውን ፈረንሣይን ስለተዋት እንደገና እ ኤ አ በ1906 ዓም ፈረንሳይን ጨምረው ሶስቱ ኃያላን የኤሮፓ መንግሥታት ትሪፓርቲት (Tripartite) አግሪሜንት የሚባለውን ውል ተፈራረሙ ። እንግሊዝ የዚያን ጊዜ እንግሊዝ ሶማሌላንድ ይባል የነበረውን ፤ ኬንያንና ሱዳንን ፤ ፈረንሣይ ጂቡቲን ፤ ኢጣሊያ የዚያን ጊዜ ኢጣሊያ ሶማሌ ላንድ ይባል የነበረውንና ኤርትራን በቅኝ ግዢነት ይዘው ኢትዮጵያን ዙርያዋን ከበዋት ነበር ። ስለዚህ ሶስቱም ከኢትዮጵያ ጋር የቅኝ ግዛት ወሰነተኞች ሲሆኑ ሁሉም ከኢትዮጵያ ጥቅም ስለነበራቸው በጥቅማቸው ምክንያት እርስ በራሳቸው እንዳይጣሉ የሚያደርጉት ውል ነው ። በውሉ ውስጥ ኢትዮጵያ እንድትገባ መጥራት ቀርቶ እንድታውቀው እንኳ አልተደረገም ። የውሉ ጉዳይ ግን የሚመለከተው በቀጥታ ኢትዮጵያን ነበር ። የጥቅም ማስከበሩ ሁኔታ በየቅኝ ግዛቶቻቸው ውስጥ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ስለሚኖራቸው ጥቅምም ጭምር ነበር ።

የሶስቱን መንግሥታት ውል ባጭሩ ብንመለከተው እንግሊዝ ከጥቁር አባይ መነሻ ጀምሮ እስከ መውጫው ኢትዮጵያና ሱዳን ወሰን ድረስ ያለው አካባቢ በኃላ ግብጽና ሱዳን በውሃው እጥረት ጉዳት ስለሚያገኛቸው ጥቅሟ የሚነካ መሆኑን ሁለቱ መንግሥታት ፈረንሣይና ኢጣሊያ አውቀው አረጋገጡላት ።

ፈረንሣይ ከጂቡቲ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋው የባቡር ሀዲድ ሥራው ቢቋረጥ ወይም ቢደከም የጂቡቲ መድከም በመሆኑ ከጂቡቲ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድ መስመር ተከትሎ ያለው ሁሉ ጥቅሟ መሆኑን እንግሊዝና ኢጣሊያ አወቁላት ።

ኢጣሊያ ፤ በመሀል ጂቡቲና እንግሊዝ ሶማሌ ጣልቃ ገብተው ሁለቱን ቅኝ ግዛቶችዋን ኤርትራንና ሞቃዲሾን ስለለዩባት እነኚህን ሁለቱን ቅኝ ግዛቶቿን ለማገናኘት በኢትዮጵያ መሀል ለመሀል አቋርጦ የሚሄድ የባቡር ሐዲድ ለመዘር

ጋት የምትችል መሆንዋን ፈረንሣይና እንግሊዝ አውቀው ተፈራረሙ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ኢትዮጵያ የተጠየቀችው ምንም ነገር የለም ።

ይህ የሶስቱ ኃያላን መንግሥታት ውል እ ኤ አ እስከ 1922 ዓም ድረስ በሥራ ላይ ቆይቶ በ1922 ዓም በውሉ ላይ ተጨማሪ አንቀጽ ገባ ። ይህም እንደገና ተከፋፍቶ የታደሰው ውል እንግሊዝ ጣና ሐይቅ አጠገብ ግድብ ለመሥራት የምትችል መሆንዋን ይፈቅድላታል ። ይህንንም ግድብ በምትሠራበት ጊዜ ኢጣሊያ እንግሊዝን በዲፕሎማቲክ መንገድ እንድትደግፋት ይወስናል ።

የኢጣሊያ መንግሥትም የተለያዩ ሁለቱን ቅኝ ግዛቶችዋን ለማገናኘት የምትሠራው የባቡር ሐዲድ ከአዲስ አበባ ከተማ ምዕራብ በኩል አልፎ እንዲሔድ ይወስንና ይህ ሐዲድ በሚዘረጋበት ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ሙሉ የዲፕሎማቲክ ድጋፉን ይሰጣል ይላል ።

ይህም ውል ለሶስት ዓመታት ያህል በተግባር ሳይውል ቆይቶ እ ኤ አ በ1925 ዓም ውሉ ዝርዝር ጉዳዮችንም ጨመረ ። ባንድ የሐዲድ ጥቅም የታሠረችው ፈረንሣይ ከውጭ ቀርታ እንግሊዝና ኢጣሊያ ውላቸውን አሻሽለው አደሱት ። የእንግሊዝ መንግሥት ጣና ሐይቅ አጠገብ ግድብ ሠርቶ ሀይቁን በሚያስፋፋበት ጊዜ ከሱዳን ወሰን አንስቶ ጣና ሐይቅ ድረስ የመኪና መንገድ ለመሥራት ሙሉ መብት ሲሰጠው ፤ ኢጣሊያ ደግሞ ሁለቱን ቅኝ ግዛቶችዋን ለማገናኘት የምትዘረጋው የባቡር ሐዲድ በትግራይና በጐንደር አልፎ አዲስ አበባን ወደ ምሥራቅ እየተወ ዳጋ ዳጋውን ይዞ ሞቃዲሾ ይገባል ይላል ። የዚህም የባቡር ሐዲድ ርዝመት 780 ማይልስ ወይም 1248 ኪሎ ሜትር እንደሚሆን ይደነግጋል ።

እጅግ በጣም የሚገርመው ነገር ኢትዮጵያ ነፃ መንግሥትና ወሰንዋን አስከብራ የምትኖር አገር ሆና ሳለች የንቀታቸው ንቀት እንግሊዝ ጣና ላይ ግድብና ከግድቡ የሚያደርስ የመኪና መንገድ ለመሥራት በሰው አገር ገብተው ባለሙሉ ሥልጣን ሆነው ሲዋዋሉ እንግሊዝ የተዋዋለው ከጣና ጌታ ከኢትዮጵያ ጋር ሳይሆን ከኢጣሊያ ጋር ነበር ።

ኢጣሊያም የባቡር ሐዲዱን በደንከል ምድር አድርጐ ጥግ ጥጉን በበረሃው ለመዘርጋት እንኳ ቢሆን ፡ ፈቃድ መጠየቅና መዋዋል ያለበት ከባለ መሬቱ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር መሆን ሲገባው ፡ እንደማይሆን ሆኖ ከአስመራ መቃዲሾ ለመሔድ በመቀሌ ፤ በጐንደር ፤ ከአዲስ አበባ ጓሮ ዞሮ ይጓዛል የሚለውን ውል ከኢትዮጵያ ጋር ሳይሆን ከእንግሊዝ ጋር ተዋዋለ ። የሁለቱም መንግሥታት አሳብ የሁለቱን መጋጨት ብቻ የሚመለከትና ሁሉም በየሆዱ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ይዞ ካላቸው የቅኝ ግዛት ጋር ለመደባለቅ ነበር ።

በዚህ ውል የተናደደ አንድ ኢትዮጵያዊ መጋቢት 8 ቀን 1919 ዓም በወጣው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ ፋሺስትና ኢትዮጵያ በሚል ርእስ "...ሙሶሎኒ ዓይኑን ከጣለባቸው አገሮች አንዱ ኢትዮጵያ ነው። እንግሊዞች ከሙሶሊኒ ጋር ሲዋዋሉ እነርሱ በጣና ባህር ሊያዙበት ፤ ሙሶሊኒ ምጥዋ አንስቶ ትግሬን ፤ ጐንደርን አድርጐ አዲስ አበባን ወደ ምሥራቅ እየተወ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የምድር ባቡር ሊሠራ ፤ ለዚኸው ሥራቸው ሁለቱም ሁሉ የኢትዮጵያን መንግሥት ፈቃድ ሊለምኑ በዚህ እርዳኝ እረዳሃለሁ ተባብለዋል ።...." በማለት ሰፊ ሐተታ ፃፈ ። ይህ ሐተታ በተፃፈበት ጊዜ የኢጣሊያ መስፍን ወደ ኢትዮጵያ መምጫ ተቃርቦ ስለነበረ መጋቢት 15 ቀን 1919 ዓም የወጣው ያው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ "ስለዱክ አብሩሲ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት" በሚል ርእስ ተነስቶ የመስፍኑን መምጣት ካተተ በኋላ "...ይህም አያራርግ የሁለቱን መንግሥቶች ወዳጅነት የሚያሰፋና የሚያፀና መሆኑን ያስረዳል ። በዚህም መካከል አንድ ሰው በመጋቢት 8 ቀን በብርሃንና ሰላም አንድ

የጋዜጣ ቃል እሳትም ስላወጣ የወጣውን ጋዜጣ የሚያነቡ አንዳንድ ሰዎች ይህ ጋዜጣ የተፃፈበት ምክንያት ሳይገባቸው ቀርቶ ተቸግረው ነበር ።

"ነገር ግን ይህን ጋዜጣ ያሳተመ ሰው ለሀገሩ እንግዳ መሆኑንና የመንግሥት ሠራተኛ አለመሆኑን…የራሱን አሳብ ጽፎ ስላሳተመ ነው እንጂ የሚበልጠው ቃል ከውጭ አገር ጋዜጣ የተገለበጠ ነው ።… እልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለጊዜው የማያስፈልግ መስሎ ስለታያቸው… የጻፈው ሰውና ያተመው የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር መቀጫ እንዲከፍሉ አዘዋል ሲሉ ሰምተናል ። ስለዚህ መጋቢት 8 ቀን የወጣው ጋዜጣ እንደቁምነገር አለመቆጠሩን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሁሉ ሳያውቁት አይቀሩም" በማለት ማስተባበያ አወጣ ። በሱማሌ የጦጥ እርሻ ያላቸው የኢጣሊያኑ ልዑል ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ምክንያት ሆኖ የወጣ መግለጫ እንጂ ነገሩ ትክክለኛ ነው ። አልጋወራሹ ቀጡ የሚለውም ለይስሙላ እንጂ እውነት ቢሆን ኖሮ "…መቀጫ እንዲከፍሉ አዘዋል ሲሉ ሰምተናል…" የሚል ቃል ተቀጣ የተባለው የጋዜጣው ዲሬክተር ባላስገባ ነበር ።

ሙሶሊኒ በቅኝ ግዛቱ በሊቢያ ውስጥ ያጋጠመው ችግር አላራምድ አለው ። እንግሊዝም ብትሆን በቱርክና በኢራክ መሀል የተነሳው የወሰን ጭቅጭቅ ቢኖርባትም በንግድ ምክር ቤቷና ኢምፓየር ኮተን ግሮዊንግ ኮርፖሬሽን ዲሬክተር የሆኑት ሰር ጀምስ ኩሪ "…የጣና ግድብ መሠራት በሱዳንና በግብጽ ውስጥ ቡዙ ጥጥ ማምረት ያስችለናል ።…" የሚል መግለጫ ሰጡ ።

በመሀሉም እንግሊዝና ኢጣሊያ በየስምምነታቸው ያለመግባባት ስለመጣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንግሊዝን ለማጥቃት ከኢጣሊያ ጋር ተወዳጁ ። በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን በ1916 ዓም የኢጣሊያን አገር ጐብኝተው ከተመለሱ በኋላም ለጉብኝት መልስ የኢጣሊያኑ ንጉሥ እጐት የሆኑት የአብሩዚ መስፍን ኢትዮጵያን እንዲጐበኙ ተደረገ ።

ፍራንክ ሐርዲ "…ምኒሊክ ቢሆን እንዲህ ዓይነቱን ችግር ይፈታው ነበር ። ተፈሪ ግን አልፈታውም ። አይፈታውምም ። በ1926 ዓም በሰኔ ወር ተፈሪ አዲስ አበባ ላለው ለብሪቲሽ ሚኒስትር 'በአገሬ ጉዳይ ኢጣሊያ ጣልቃ እየገባ የሚያስቸግረኝን ያህል እንግሊዞች አያስቸግሩም' ብለው ከነገሩት በኋላ ለኢጣሊያው ሚኒስትር ደግሞ 'ሙሶሊኒ የተከበሩ ሰው ናቸው ። በአመራራቸውም እንተማመናለን' ብለው ነገሩት ። በዚያው ዕለት ደግሞ 'እንግሊዝና ኢጣሊያ በ1925 ዓም ያደረጉትን የሕብረት ስምምነት እንቃወማለን' በማለት ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ ዋና ፀሐፊ ደብዳቤ ላኩ። …ሙሶሊኒም ተፈሪ ምን ያህል ታማኝ ነው፣ እያለ ይጠይቅ ጀመር…" በማለት አትቷል ። ዘመኑ እ ኤ አ ነው ።

ኢትዮጵያ ከኢጣሊያ ጋር ወዳጅነት እንደጀመረች በ1927 ዓም እ ኤ አ ሙሶሊኒ አዲስ አበባ ላለው ሚኒስትሩ 'የእንግሊዞችን ድጋፍ በመጠኑ አድርገህ ! ስለ ኢትዮጵያ ጥቅም ተከራከር' አለው ። በዚህ ጊዜ እንግሊዞች የጣናን ግድብ እንሥራ ብለው የኢትዮጵያን መንግሥት ጠየቁ ።

የኢትዮጵያ መንግሥትም "ግድቡን የኢትዮጵያ መንግሥት ያሠራዋል ። መንግሥት የማይችለው ቢሆን ደግሞ ኩባንያ ያቋቁማል ። የዚያን ጊዜ እንግሊዞች ሼር ሊገዙ ይችላሉ" ብሎ በመስከረም ወር መልስ ሰጠ ።

በ1919 ዓም በግንቦት ወር የአብሩዚ መስፍን ለጉብኝት አዲስ አበባ በመጡ ጊዜም ከአሰብ እስከ ደሴ ኢጣሊያ መንገድ ሊሠራ ንግግር ተደረገ ። ከሁለት ዓመት በኋላ በ1921 ዓም አልጋወራሽ ተፈሪ ከአሰብ እስከ ደሴ ያለው የመንገድ ሥራ ለዳች ተቋራጭ መስጠቱን አሳወቁ ። ይህን ሲያሳውቁም "…በወሰን መሀል ሆነው የሚያስቸግሩትን ሽፍቶች ለማጥፋት ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢጣሊያ መን

ግሥት ጋር የሰላም ወዳጅነት ውል ለመፈራረም ፈቃደኛ ነው...” በማለት ገለጡ። ሙሶሊኒም ስለመንገዱ ሥራ የነበረው ንግግር መፍረስ ቢያስቀይመውም ጊዜው እስኪሞላለት ድረስ ያን ትቶ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ሐምሌ 26 ቀን 1921 ዓም “...ወደፊት የሚሠሩ መንገዶች ለኢጣሊያ ይሰጣሉ...” የሚል የወዳጅነትና የሰላም ውል ተዋዋሉ።

ኢጣሊያና ኢትዮጵያ በዚህ የወረቀት ወዳጅነት ላይ እንዳሉ ሶስቱ ኃያላን መንግሥታት ፈረንሣይ፣ እንግሊዝና ኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ እንዳ ይገባ የሚወስን እ ኤ አ በ1930 ዓም ተዋዋሉ። በኤርትራ፣ በጂቡቲ፣ በእንግሊዝ ሶማሌ፣ በኢጣሊያ ሶማሌ፣ በኬንያና በሱዳን በኩል ወደኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ እንዳይገባ ወስነው ሲዋዋሉ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የተወሰነ ጥይትና ጠመንጃ ብቻ ለመግባት እንዲፈቀድ ተዋዋሉ።

ከዚህ ውል ቀደም ብሎ በ1920 ዓም ኢጣሊያ በኦጋዴን ውስጥ በግጦሽ ሣርና በውሃ ምክንያት ወሰንዋን በወታደር አጥራ ነበር። በተለይ የኢትዮጵያ ግዛት ከሆ ነው ወልወል ላይ ብዙ የውሃ ጉድጓዶች ስለነበሩ ኢጣሊያ ወሰን አልፋ ወልወልን ያዘች። ወዲያውኑም ሙሶሊኒ የኢጣሊያን ሕዝብ ሰብስቦ “...ኢጣሊያ በምሥራቅ አፍሪካ ያላትን ቅኝ ግዛቶች ኤርትራንና ሶማሊያን በጦር ኃይል ለመውሰድ ኢትዮ ጵያ ጦሯን እያደራጀታለች። እኛም ብንሆን በጦርነት ሳንጋጠም ቅኝ ግዛቶቻችንን እጃችንን አጣምረን እያየን የምንለቅ አይደለንም። ስለዚህ አገርህን የምትወድ ኢጣ ሊያዊ ሁሉ ተነስ...” አለ።

## የወልወል ግጭት

የኢጣሊያ ንጉሥ ሳልሳዊ አማኑኤል በመስከረም ወር 1925 ዓም ኤርትራን በጎበኙ ጊዜ ጀኔራል ዲቦኖን “ስማ ዲቦኖ፣ እለፍ፣ ያለምንም ችግር ተራምደህ እለፍ” አሉት። የኢጣሊያ ጦርም ወደ ኤርትራ ይጓዝ ጀመር። እ ኤ አ ከ1932 ዓም እስከ 1933 ዓም ድረስም 65 000 ወታደሮች ያሉ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት በነበረ ችው ኤርትራ ውስጥ ተከማቹ። አሁንም እ ኤ አ በኅዳር ወር 34 ዓም ደቦኖ ከኢ ጣሊያ ንጉሥ ጋር ወደ ሶማሊያ ሄዶ የጦርነቱን ሁኔታ አዘጋጀ። የኢጣሊያ ጦር ሚኒስትርም ወደ ኤርትራ መጥቶ በኤርትራ የተዘጋጀውን ጦር ከተመለከተ በኋላ ለሙሶሊኒ ሪፖርት አቀረበ። ሙሶሊኒም ለጦር ሚኒስትሩ “ኢትዮጵያን ለመውጋት በዚያ በኤርትራ ተዘጋጅቷል ያልከኝ ጦር በቂ ነው ብትልም አይበቃም እላለሁና ብዙ መድፍ ጨምርላቸው” አለው።

ደቦኖ በፃፈው መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልጽ “...ሙሶሊኒ ዘንድ ቀረብኩና ስማኝ አልኩት። የጦርነቱን ጉዳይ በኔ ላይ የምትጥልብኝ ከሆነ የጠቅላላው የጦር ነቱ የበላይ አላፊ አድርገኝ አልኩት። ዱቼም ትኩር ብሎ አየኝና ‘በእርግጥ ትሆና ለህ ?’ አለኝ።

እኔም ‘በጣም ያረጀሁ አልመስልህም’ አልኩት

ሙሶሊኒም፣ ‘የለም፣ ይልቅስ ጊዜ አናጥፋ። ነገሩን ማንም ሳይሰማው በሚስጢር ያዘውና ለምሥራቅ አፍሪካው ጦርነት ተዘጋጅ’ አለኝ።

እኔም ‘ከመሬት ተነስተን ያለ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ብናውጅ ፖለቲካው አይበላሽብንም ወይ’ አልኩት።

ሙሶሊኒም፣ ‘ዝም በል። አንተ ያለብህ በሙሉ ኃይል ወደፊት መግፋት ነው’ አለኝ።

'ገንዘብስ?' አልኩት

'ሞልቷል ፤ ስለገንዘብ አታስብ' አለኝ...በደንብ ከተዘጋጀሁ በኋላም የጦርነቱ ሰበብ ወልወል ላይ እንዲጀመር ሆነ..." ሲል ጽፏል ።

ወልወል በሐረርጌ ክፍለ ሀገር በኦጋዴን ውርጭ የሚገኝ የኢትዮጵያ መሬት ነው ። ኢትዮጵያና ዛሬ ሶማሊያ የሆነውን አካባቢ በቅኝ ግዛትነት ይዛ የነበረችው እንግሊዝ ወሰናቸውን በመሬቱ ላይ ሆነው እያመለከቱ ለመካለል ተስማምተው ወሰን ተካላዮች ላኩ ። የክልሉም ስምምነት ሥራ በ1889 ዓም ግንቦት 28 ቀን በተደረገው ውል መሠረት ነበር ። ተካላዮቹ የወሰኑን መስመሮች ከተመለከቱ በኋላ የእንግሊዝ መልእክተኞች "የግጦሹን ሥፍራ በሁለቱም ወገን እየዞርን እንጎብኘው ። በኛ በኩል ግን እስከ ባህሩ ድረስ እየተጓዳኙ ኢትዮጵያውያን ከብቶቻቸውን ቢያግጡ አንቃወምም" ሲሉ አሳብ አቀረቡ ።

እንግሊዞቹ ይህን አሳብ ማቅረባቸው ጠቃሚ የግጦሽ ስፍራ የሚገኘው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መሆኑን ያውቁ ስለነበረ በነሱ አስተሳሰብ መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥትም ግጦሹን እንዲፈቅድ ነበር ። የኢትዮጵያ መልእክተኞች የግጦሹን ሥፍራ እየዞሩ ከማየት ይልቅ በየጉሣው እየጠየቁ በካርታው ላይ በማመልከት ጉዳዩ ፍጻሜ እንዲያገኝ ለእንግሊዝ መልእክተኞች አሳሰቡ ። የኢትዮጵያ መልእክተኞች ይህን አሳብ ያቀረቡበት ሁለት ምክንያቶች አሉዋቸው ። 1ኛው ፤ የግጦሽ ሥፍራ የሚባለው ከወልወል በታች ባለው በጋለዱ ወረዳና በኢጣሊያኖች ወሰን አጠገብ ያለው በመሆኑ ዞሮ ማየት የማያስፈልግ መሆኑን በማወቅ ሲሆን ፤ 2ኛው ምክንያታቸው ፤ ኢጣሊያኖች ከኢትዮጵያ ጋር ጠብ ለማንሳት ፍላጎት ስላላቸው በዚያ ሳቢያ እምባጓሮ እንዳይነሳ በመፍራት ነበር ። ዳሩ ግን የእንግሊዝ መልእክተኞች ደጋግመው በመጠየቃቸው ኅዳር 10 ቀን 1927 ዓም ከጂጂጋ ተነስተው ወደ ኦጋዴን ተጓዙ ።

ወሰን ተካላዮችንም እንዲያጅቡ የጉርሱም አቢጋዝ ፊታውራሪ አለማየሁና የጂጂጋው አቢጋዝ ፊታውራሪ ሽፈራው ታዘው አብረው ሄዱ ። ወሰን ተካላዮቹ በደገሀቡርና በአዋሬ ፤ በገሮና በአዶ በኩል አልፈው ኅዳር 14 ቀን ወልወል ደረሱ ።

ወልወል 359 የውሃ ጉድጓዶች ያለበት ሥፍራ ነው ። የእያንዳንዱ ጉድጓድ ርዝመትም እስከ 50 ሜትር የሚደርስ ነው ። እነዚህን ጉድጓዶች ያስቆፈሩ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ናቸው እያሉ ያገሬው ሽማግሌዎች ይናገራሉ ።

ሙሶሊኒ ቀደም ብሎ ለኢጣሊያ ሶማሊያ ቅኝ ግዛት ገዢ ባስተላለፈው ትእዛዝ ሙስታሂል ፤ የዋቢ ሸበሌ አካባቢ ፤ ጉድጓዶቹ ያሉበት ወልወል በሙሉ ፤ ዋርዴር ፤ ገርሎጉቢ ፤ ቆራሄ ፤ ቀብሪደሃርና የፋፋን አካባቢ በሙሉ በኢጣሊያ ወታደር እንዲያዝ አዝዞ ስለነበረ የኢጣሊያ ባንዳ ወሰን አልፎ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወልወል ላይ ሰፍሮ ተገኘ ።

እዚህ ላይ የኢጣሊያው ጦር አዛዥ ጀኔራል ደቦኖ ስለ ኢትዮጵያ ጦርነት ከጻፈው መጽሐፉ ጥቂት እንጥቀስ ። "...ቢኖር ሙሶሊኒ በአስቸኳይ ወሰን እያለፍን ገፍተን እንድንይዝ አዝዞ በኦጋዴን በኩል የኢትዮጵያን ወሰን አልፈን ያዝን ። ሊቢያውያንን አሸንፈን ሊቢያ ቅኝ ግዛታችን ብትሆንም ሊቢያንም ቢሆን በቀላሉ አልያዝነውም ። የኢትዮጵያውያን ደግሞ የበለጠ ነገር መሆኑን እናውቃለን ። ኢትዮጵያውያንን ለማሸነፍ ጦርነት ብቻ በቂ አይደለም ። ኃይለኛ ፕሮፓጋንዳ ያስፈልገን ነበር ። ለዚህም ለፕሮፓጋንዳው ሥራ ገንዘብ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ጉዳዩን ገልጬ ብዙ ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ለሙሶሊኒ አመለከትሁ ። ሙሶሊኒም የገንዘብ እጥረት የለብንምና በርታ ሲል እንደገና መልስ ሰጠኝ..." ብሏል ።

የሞቃዲሾው የኢጣሊያ ሶማሊያ ገዥ የነበረው ራፒ በየአቅጣጫው ጦርነቱን እንዲመራ በደቦና ታዘዘ ። የሞቃዲሾው ገዥ ራፒ ደግሞ የባንዳውን ብርጌድ አዛዥ

ካፒቴን ሮቤርቶ ቺማሩታ ጦሩን እንዲያንቀሳቅስ አዘዘው ። ለዚህ ጠብ ፍለጋ ካፒቴን ሮቤርቶ የተመረጠው በሶማሊያ ግዛት ውስጥ በክፉት ዘራፊነቱ ፤ በጭካኔውና በጀብደኛነቱ የታወቀ ሰው ስለነበረ ነው ።

የኢጣሊያ ባንዳ ጦር እንደተንቀሳቀሰ አንድ ትእዛዝ ወይም አዋጅ ከሮም ተላለፈ ። "ማንኛውም የኢጣሊያ ወታደር የረገጠው መሬት ሁሉ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት መሆን አለበት ። በምኒሊክ ጊዜ በ1896 ዓም እና ግንቦት 16 ቀን 1908 ዓም ከኢትዮጵያ ጋር የተደረገው የወሰን ስምምነት መፍረሱን የኢጣሊያ ሹማምንት ሁሉ እንዲያውቁት " የሚል ነበር ። ከዚህ አዋጅ በኋላ እ ኤ አ በ1934 ዓም በነሐሴ ወር የኢጣሊያ ባንዳ ወሰን አልፎ ዋርዴርና ወልወል ላይ ሠፈረ ። እ ኤ አ በ1908 ዓም በተደረገው የወሰን ስምምነት መሠረት ወልወል ከወሰን 96 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ የሚርቅ የኢትዮጵያ መሬት ነው ።

ኅዳር 14 ቀን 1927 ዓም የኢትዮጵያና የእንግሊዝ የወሰን ኮሚሽን ወልወል ደረሰ ። ወልወል ላይ 250 የኢጣልያ ባንዳዎች ለጦርነት በሙሉ ትጥቅ ተሰልፈው ወሰን ተካላዮቹን አቆሙዋቸው ። ወልወል ላይ የተተከለውን የኢጣሊያን ባንዲራ እንዳያልፉም አስጠነቀቋቸው ። ወሰን ተካላዮቹን አጅበው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ግን የኢጣሊያኖቹን ባንዳ አልፈው ጉድጓዶቹን ለመያዝ አፈጠጡ ። በበረሃው ጉዞ ምክንያት ለሰውም ሆነ ለእንስሶች ውሃ ያስፈልግ ነበርና ነው ። ግን የእንግሊዞችና የኢትዮጵያውያኑም ሹማምንት ጠብ እንዳይነሳ በማለት የኢትዮጵያን ወታደር በትእዛዝ ብቻ ሳይሆን በልመናም ጭምር ንዴቱን አበረዱት ።

የኢትዮጵያ ወታደር ፤ ትእዛዝ በማክበር ወደፊት መግፋቱን ይተው እንጂ ከቆመበት ሥፍራ አልንቀሳቀስም አለ ። የኢጣሊያ ባንዳና የኢትዮጵያ ወታደር ተፋጦ የቆመበት ቦታ አንዳንዱ ሥፍራ ብቻ የአምስት ሜትር ስፋት ሲኖረው የተቀረው በሙሉ ሁለት ሜትር ርቀት ብቻ ያለው ነበር ። በዚህ ርቀት ተፋጠው ቀኑን ውለው ሌሊቱን አነጉ ። እንዲያውም ሌሊቱን ባንዳዎቹን እያለፉ ሄደው ኢጣሊያኖች ከያዙዋቸው ጉድጓዶች ውሃ ቀድተው ተመለሱ ። ይህ ሁኔታ እንግሊዞቹ በተንቀሳቃሽ ፊልም የቀረፁትና ለእንግሊዝ ሕዝብ ያሳዩት በመሆኑ የኢትዮጵያውያኑ ጀግንነትና ልበ ሙሉነት ለአገራቸውም ምን ያህል ፍቅር እንዳላቸው የእንግሊዝን ሕዝብ ሲያስደንቅ ሰንብቷል ። በጊዜውም ብዙ የእንግሊዝ ጋዜጦች ይህንኑ የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት እያደነቁ ጽፈዋል ።

የእንግሊዞቹ ወሰን ተካላዮች ሹም ኮሎኔል ክሊፎርድ ስለዚያች ቀን ሁኔታ ለጋዜጠኞች ሲገልጡ "....ጥቂት የሆኑት የኢትዮጵያ ወታደሮች ልመናችንን ሰምተው ባይቆሙ ኖሮ የወሰናቸውን መደፈር ሲያዩ ደማቸው እንደፈላ ቢለቀቁ ፤ አንድም ባንዳ በወልወል ምድር ላይ በሕይወት አይገኝም ነበር ። እኛም በኋላ እንዳጠናነው ሁላችንም በነጋታው በኢጣሊያ አይሮፕላን ተደብድበን እናልቅ ነበር...." ብለዋል ። አሁን ወደ ነበርንበት እንመለስ ።

የኢትዮጵያ ወታደሮችና የኢጣሊያኖቹ ባንዳዎች ወልወል ላይ ተፋጠው ካደሩ በኋላ በማግሥቱ ኢትዮጵያውያኑ በግዴታ ውሃ ሲቀዱ ማደራቸው እንደተሰማ የባንዳዎቹ አዛዥ ካፒቴን ሮቤርቶ ቺማሩታ ለወሰን ተካላዮች ማስጠንቀቂያ ላከ ። እዚህ ላይ የምገልፀው ፤ ባንዳ የሚለው ቃል የኔ አጠራር ሳይሆን የኢጣሊያው የእግረኛው ጦር ክፍል በኢጣሊያኖቹ ዘንድ የባንዳ ብርጌድ ይባል ስለነበረ እነሱው ያወጡለት ስም ነው ።

የእንግሊዙ ዳኛ ኮሎኔል ክሊፎርድና የኢትዮጵያው ተካላይ ደጃዝማች ተሰማ ባንቴ ባንድነት የኢጣልያ ወታደሮች ወሰን አልፈው በመያዛቸውና ወደነባሩ ወሰን እንዲመለሱ የተቃውሞና የማሳሰቢያ ደብዳቤ ዋርዴር ላለው ለካፒቴን ሮቤርቶ ቺማሩታ ላኩለት ። ሮቤርቶም "....በወሰን ተካላዮችና በባንዳው መካከል ጠብ እንዳ

ይፈጠር ስለምፈልግ የኛ ወታደር ካለበት እንዳይንቀሳቀስ አዝዣለሁና እናንተም አሁን ካላችሁበት ቦታ የወሰኑን ምልክት አድርጋችሁ ተመለሱ ። የወሰኑም ቦታ በሁለቱ ዛፎች መካከል ይሠመር...” የሚል መልስ ላከ ።

ሮቤርቶ ይህን ደብዳቤ ከላከ በኋላ በማግሥቱ ወልወል ላይ ያለውን ወታደሩን ጉብኝቶ ከወሰን ተካላዮቹ ጋር ተገናኘ ። ወሰን ተካላዮቹም ወሰን አልፎ መያዙን ነገሩት ። ሮቤርቶም ‘ካለሁበት ቦታ ንቅንቅ አልልም ። ስለውሃው ከሆነ የኢትዮጵያ ሰዎች በኛ ፈቃድ ከወታደሮቻችን ኋላ ሄደው መቅዳት ይችላሉ ። አልፈው በሚሄዱበትም ጊዜ እንዳችም መሣሪያ እንዳይዙ በኛ ወታደሮች እየተፈተሹ ያልፋሉ” ካለ በኋላ ንዴቱንና ጥጋቡን ለመግለጽ ተነስቶ ይንጐራደድ ጀመር ። ወዲያው ሁለት የኢጣሊያ አይሮፕላኖች በወሰን ተካላዩ ላይ አንገዠበቡ ። ከዚያ አለፍ እያሉም የመትረየስ ተኩስ አሰሙ ። በኢትዮጵያ ወታደር ላይም ዝቅ ብለው በማንዣበብ የኢጣሊያን ባንዲራ እያሳዩ አለፉ ። የዚያን ጊዜውን ዝርዝር ሁኔታም በዚያው በቦታው የነበሩት የእንግሊዝ ወሰን ተካላዮች ማለት ካፒቴን ተይለር ፤ መቶ አለቃ ኪሊን ግውድ ፤ ሚስተር ኩርልና 50 አለቃ ግራቨስ እያንዳንዳቸው በሰፊው በመዘርዘር የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል ። ለካፒቴን ሮቤርቶ ቺማሩታም አድራጎቱ ትክክል ያለመሆኑን ወዲያውኑ ነግረውታል ።

የእንግሊዙ ዋና ዳኛ የነበረው ሌ/ኰሎኔል ክሊፎርድ እ ኤ አ ኅዳር 24 በተፃፈ ደብዳቤ ኢጣሊያ ወሰን አልፋ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መግባቷንና የኢንተርናሽናልን ሕግ በመጣስ ለጠብ ፍለጋ በሌላ መንግሥት አገር ላይ የጦር አይሮፕላን መላኳን በመቃወም አስታውቆ ኮሚሽኑ አደጋ እንዳይደርስበት ከወልወል ጥቂት ፈቀቅ ብሎ አዶ ላይ ለመስፈር መገደዱን ለእንግሊዝ መንግሥት ሲገልጽ በግልባጭም ለኢትዮጵያ መንግሥት አሳወቀ ።

የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ግን በወልወልና ግራዝማች አፈወርቅ (በኋላ ደጃዝማች የተባሉት) ባሉበት በገርሎጉቢ እየተመላለሱ ያስፈራሩ ጀመር ። በኋላም የኢጣሊያው ጦር አዛዥ ካፒቴን ሮቤርቶ ለደጃዝማች ተሰማ ባንቲ አንድ ደብዳቤ ፃፈ ። እ ኤ አ ታህሳስ 4 ቀን የተጻፈው ደብዳቤውም እንዲህ ይላል ፦“...የመረጃ ክፍሎች እንደነገሩኝ የኢትዮጵያ ወታደር ሌሊት ባንዳዎች ያሉበትን ወሰን ጥሶ ለማግባት ከባድ ዝግጅት ማድረጉን ሰምቻለሁ ። ተጠንቀቁ ። ያለዚያ ለታላቁ የኢጣሊያ ንጉሥ ክብር ስል ለመዋጋትና እናንተን ለመመለስ መቁረጤን ይወቁት...” ሲል ላከ ።

በማግሥቱ ኅዳር 26 ቀን ረቡዕ ልክ ከቀኑ 9 ሰዓት ተኩል ሲሆን በድንገት ባንዳዎቹ በኢትዮጵያ ወታደር ላይ አደጋ ጣሉ ። ወዲያው በሰማይ አይሮፕላኖች ፤ በምድር ታንኮች ደርሰው በባንዳዎቹ መድፍና ቦምብ መሬቲቱ ተርገበገበች ። ኢትዮጵያውያኑም ያሉበትን ሥፍራ ሳይለቁ ባላቸው አሮጌ መሣሪያ እስከ ሌሊቱ 5 ሰዓት ድረስ በጀግንነት ተዋጉ ። በዚያም ጦርነት 94 ኢትዮጵያውያን በጀግንነት ሲወድቁ 45 ቆሰሉ ። በጦር መሪዎቹ ትእዛዝም በጦር ሜዳው የሞቱትን የፊታውራሪ አለማየሁን አስከሬን ይዘው ወደ አዶ አፈገፈጉ ።

እዚያ ጦርነት ላይ የጀግንነት ሞያ ከሠሩት መሀል ብዙዎቹን መጥቀስ ቢቻልም የአሊ ኑርን ጀግንነት ሳላነሳው አላልፍም ። የወላይታ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆነው አሊ ኑር ቀደም ብሎ አገሬን ጠላት አይረግጣትም ፤ የአገሬ የኢትዮጵያም ወሰን አይደፈርም ። ለአገራችን ለኢትዮጵያ እንሞታለን ፤ እኛ ሳናልቅ አገራችን ኢትዮጵያ በጠላት አትያዝም ብሎ ፎክሮ ነበርና ሠራዊቱን ይዞ በተሰለፈበት አካባቢ የወልወሉ ግጭት ዕለት 37 ባንዳዎች ገድሎ ለበላይ አለቃዎቹ ግዳይ ጥሏል ።

በወልወሉ ግጭት እለት 127 ባንዳዎች ሲገደሉ ከባላምባራስ አሊ ኑር ግንባር ሌላ ፤ በሌላ አቅጣጫ የተገደሉት 90 ባንዳዎች ናቸው ። ባላምባራስ አሊ ኑር እና በስሩ የሚመራው ጦር በወልወል ግጭት ጊዜ በሠሩት ሞያ የውጭ ታሪክ ፀሐፊዎች


በግቸውን መዝግበውላቸዋል ። እንግሊዛዊው ሙቶ አለቃ ክሊንግውድ የወልወልን ግጭትና የኢጣሊያን የግፍ አሠራር በፊልም ቀርጾት ስለነበረ ፊልሙ ለንደን እንደገባ በእንግሊዝ ሕዝብ ዘንድ በአድናቆትና በኀዘን ለብዙ ቀናት ሲታይ ከረመ ።

ኮንፍሊት ኢታሎ ኢትዮፒየን በሚለው መጽሐፉ ፕራዲሊ እንደፃፈው "...የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ከወልወሉ ግጭት አልፈው ገርለጐቢ በመሄድ በዚያ ያለውን የኢትዮጵያን ጦር በቦምብ ደበደቡ ። በቦታው ከነበሩት አሥር ድንኳኖችም ስድስቱ በአይሮፕላን ቦምብ ተቃጠሉ ። ግራዝማች አፈወርቅም ተመቱ ..." ብሏል ። ዝርዝሩ አፈወርቅ ታሪክ ውስጥ አለ ።


የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ይህን የኢጣሊያን አድራጎት በመቃወም አዲስ አበባ ከተማ ላለው የኢጣሊያ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ለሲኞር ሞምቢሊ በደብዳቤ ገለጡ ። ጉዳይ ፈጻሚው ሞምቢሊም ለተላከለት የተቃውሞ ደብዳቤ መልሱን እንዲህ ሲል ላከ ። "...ጥፋቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ነው ። ወታደሮቻችሁ 30 ወታደሮች (ኢጣሊያውያን) ገድለውብናል ። የኢጣሊያ መንግሥትም ከኢትዮጵያ መንግሥት ካሣ ይጠይቃል ። ካሣውን ብቻ ሣይሆንም ይቅርታ እንድትጠይቁን እንፈልጋለን ። ከመንግሥቴ በታዘዝኩት መሠረትም ለደረሰብን ኪሣራና ድፍረት ፣ 1ኛ ፤ የሐረርጌው ገዥ ደጃዝማች ገብረ ማርያም በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ወልወል ድረስ እንዲሄዱና በዚያ ያሉትን የኢጣሊያ ጦር አዛዦችን ይቅርታ እንዲጠይቁ ፤ በዚያው ጊዜም አንድ የኢትዮጵያ የክብር ዘብ በዚያ ለተሰቀለው ለኢጣሊያ ባንዲራ ክብር ተሰልፎ ሰላምታ እንዲሰጥ ፤ 2ኛ ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ላባየው ድፍረትና ላደረገው ጥፋት ለሞቱብንና ለቆሰሉብን ሰዎች ካሣና ለፈረሰው ምሽጋችን ማሠሪያ 200,000 የማሪትሬዛ ብር ካሣ እንዲከፍል ፤ 3ኛ ፤ ለግጭቱ መነሻ ምክንያት የሆኑት ሹማምንቶች ከሥልጣናቸው ተሽረው እንዲታሰሩ ፤ መታሰር ብቻ ሳይሆን የኢጣሊያን ባንዲራ ታላቅነት አምነው በይፋ እንዲናገሩና በአለቸኳይ እንዲቀጡ..." የሚል መልስ ላከ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢጣሊያ መንግሥት የቀረበውን ሐሳብ እንዱንም ሳይቀበል ጉዳዩ በሊግ ኦፍ ኔሽንስ እንዲታይ ክስ አቀረበ ። በየጊዜው የተሰበሰበው ጉባዔና ለዚሁ ጉዳይ የተመረጡት ዳኞችም የኢጣሊያ መንግሥት ማጥቃቱንና ኢትዮጵያ መጠቃትዋን አምነው ፤ ጃፓን ፤ ማንቹሪያ ላይ ባደረገችው ጥፋት ማኅበሩ ማለት ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ቢያወግዛት ማኅበሩን ጥላ እንደወጣች ሁሉ አሁንም ኢጣሊያን ብናወግዝ ማኅበሩን ጥሎ ይወጣል በማለት ስለፈሩ ኢትዮጵያ መበደሏን እያመኑ እንዳችም እርዳታና ድጋፌ ውሳኔ እንዳይሰጧት ነገሩን በማድበስበስ ቆዩ ። ጦርነቱም በኢትዮጵያ ምድር እየተካሄደ ስለነበረ በ28 ዓም ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር የሰሜን ጦርዋን አንቀሳቀሰች ።

ደቦኖ እ ኤ አ ጥር 7 ቀን 1935 ዓም ከኔፐልስ ወደ አፍሪካ ከመምጣቱ በፊት ሮም ላይ ከሙሶሊኒ ጋር ተገናኝቶ ነበር ። ሙሶሊኒ ፤ ደቦኖን ተቀብሎ ሲያነጋግር "...አሁን እንግዲህ የምሥራቅ አፍሪካ ዋና ኮሚሽነር ሆነህ ተሾመሃል ። በወልወል ላይ በሠራኸው ታላቅ ሥራ ተመስግነሃል ። ለሥራህ በቂ ነው ባይባልም ኒሻን ተሸልመሃል ። ትልቁ ሽልማት ግን ወደፊት ይጠብቅሃልና ግፋ" አለው ።




የወልወል ጉድጓዶች ።



የወልወሉ የኢጣሊያኖች ምሽግ ከአይሮፕላን ላይ ሲታይ ።



ዳቢ  ሸበሌ አካባቢ የደጃዝማች ገብረ ማርያም ሠፈር በኢጣሊያ ሰላይ አይሮፕላን የተነሳው ፎቶግራፍ ።



ዋርዴር ላይ በነበረው የኢጣሊያ ጦር ሠፈር የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ሠፍረው ።



ለወልወሉ ግጭት የኢጣሊያ ታንኮች ሲጓኑ ።



የወልወሉ እልቂት

## አፈወርቅ

የቆራሄው ጀግና ደጃዝማች አፈወርቅ ሲባል ብዙ ሰው ያውቃል ። እንደሌላዎቹ ጀግኖቻችን ሁሉ ደጃዝማች አፈወርቅ በዝና ጀግና ይባላሉ እንጂ ታሪካቸው አል ተወራም ። ተግባራቸውንም የሚያውቁላቸው በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው ። ለብዙ ዎች የውሸት ታሪክ ሲነገር የደጃዝማች አፈወርቅ ግን እውነተኛውም አልተነገረላ ቸው ።

ጆርጅ እስቲር ስለአፈወርቅ ሲገልጽ "…አፈወርቅ ጨዋና መልካም አስተዳ ዳሪ ነው ። በኦጋዴን ውስጥ የወታደር ካምፖችን በሚገባ ያደራጀ ነው ። የወታደሩ ጤና እንዲጠበቅና ዘመናዊ መገናኛ እንዲኖረው ያደረገና የኦጋዴን ኑሮ አስደሳች እንዲሆን የፈጠረ አፈወርቅ ነው…" ይሉላቸዋል ።

የአፈወርቅ መቀመጫ ቆራሄ ላይ ነበር ። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር በተ ነሳች ጊዜ በኦጋዴን ጦር ሜዳ ከአፈወርቅ ወልደ ሰማዕት ጋር የነበረው እስቲር ስለ ደጃዝማች አፈወርቅ ከጻፈው በጥቂቱ እንመልከት ።

"…በአፈወርቅ ጦር ካምፕ ግቢ ውስጥ አንድ ረጅምና ትልቅ ዛፍ አለ ። ዛፉ የአካባቢውን ሙቀት በረድ ያደርገዋል ። አፈወርቅ ከዚያ ዛፍ ሥር መቀመጥ ይወዳሉ ።

"አፈወርቅ በፎቶግራፋቸው ከሚታዩ ይልቅ በቁመናቸው ሲታዩ የተለዩ ናቸው ። ባሁኑ ጊዜ አፈወርቅ መናኛ የኢትዮጵያውያን መኰንን የጦር ልብስ ለብሰዋል ። ለችሎት ከሚለብሱት ልብስ ይልቅ ይሄኛው ያምርባቸዋል ። እንደ ጃፓኖች አለባ በስ ግልድም ነው ያገለደሙት ። ጫማቸው የሱማሌዎች ሰንደል ጫማ ነው ። በጉናቸው ትልቅ ሽጉጥ ታጥቀዋል ። ካየኋቸው ሹማምንት ሁሉ አፈወርቅ የተለዩ ናቸው ። ጥቁሩ ያይናቸው ሽፋል አይናቸውን ዞሮ ከቦታል ። ሲጫወቱ ያን ከባድ አንገታቸውን ማነቃነቅ ይወዳሉ ።…" በማለት እስቲር ስለ አፈወርቅ ሁኔታ ይተነትናል ።

ለኢትዮጵያ ባዕድ የሆነው እስቲር ስለ ኢትዮጵያዊው ጀግና ሲመሰክር "…ከቀኑ 12 ሰዓት ተኩል ሲሆን የተለመደው የለሊት ጥበቃው ትእዛዝ ይሰጣል። በገርለጉቢ እና በቀብሪ ደሀር ስለሚደረገው ጥበቃ ሁሉ ይነገራል ። አፈወርቅ ይህን ትእዛዝ በሚሰጡበት ጊዜ ጭፍሮቻቸው ትእዛዙን ያለመሰልቸት መቀበላቸውን ይቆጣጠራሉ ።…ከዚያም አፈወርቅ በያንዳንዱ ሰዓት በራዲዮ ግንኙነት የዓለምን ዜናና የወታደሮችን ሁኔታ ይከታተላሉ ።" ካለ በኋላ "በቆራሄ ጦር ሠፈር ያሉዋ ቸው ወታደሮች 600 ናቸው ። አፈወርቅ እንዳጫወቱኝ የቆራሄው ጦር ሠፈር ከተ ደጳመ ሶስት ሳምንት ነው ። ዋናው ጦር ሠፈር ገርለጉቢ ነው ። በነሐሴ ወር ውስጥ ኢጣሊያ ከገርለጉቢ ደቡብ በኩል ወሰን አልፎ ሊገባ ግሰቡ ስለተሰማ አፈወርቅ በዚህ በኩል ያለውን ተጠንቅቀው ይጠባበቃሉ ።

"በነሐሴ ወር 600 የሱማሌ ባንዳ ጭፍራ ያለው ሁሴን አሊ በቆራሄ ያሉትን የውሃ ጉድጓዶች የያዘ እንደሆነ ኢጣሊያ ብዙ መትረየሶችንና ቢያስፈልግም ታንክ ጭምር ለመስጠት ቃል መግባትዋንና ማባበልዋን አፈወርቅ ሰምተዋል ። ከዚህም ሌላ ኢጣሊያኖች ወሰን አልፈው መግባት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ጦር ከጂጂጋ ጋር የሚገናኝበትን መንገድ ቆርጠው ለመያዝ ፕላን ማድረጋቸውንም አፈወርቅ

ያውቃሉ ። ስለዚህም ጉዳይ አፈወርቅ ሲናገሩ "...አሳባቸው ምግብም እንዳናገኝና በረሃብ ምክንያት የጦር ሠፈራችንን እንድንለቅ ለማድረግ ነው ። እስቲ ግድየለም ፤ እናያቸዋለን' ብለውኛል ። እዶ ፤ ዳኖት እና መርሲ ያሉት የኢትዮጵያ ወታደሮች በውሃ እጦት ምክንያት ቦታውን እየለቀቁ ወጥተዋል" በማለት ጽፏል ።

የዚያን ጊዜው የአፈወርቅ ወልደሰማዕት ማዕረግ ግራዝማችነት ነው ። ደጃዝማች የተባሉት ከሞቱ በኋላ ነው ። ወደ እስቲር ጽሁፍ እንመለስ ። እንዲህ ይላል ።"...ከአፈወርቅ ጋር ስንጫወት 'ተመልከት ከዚያ ማዶ' አሉኝና ስመለከት የሙላህን ምሽግ አየሁ ። ዙርያውን በደህና ግንብ የተገነባ ነው ። በምሽጉ መሀል ፀረ አይሮፕላን የሆነ ኦርሊኮን ተጠምዶ አየሁ ። ኦርሊኮኑን እንዳየሁ አፈወርቅ በኩራት 'ይሄውልህ ፤ እሱ የኔ ነው' አሉኝና ስለሙላህ ሲያጫውቱኝ 'ሙላህ እዚህ ቦታ የመጣው እናንተ ከጀርመን ጋር ያደረጋችሁት ጦርነት ማለቂያው ላይ ነው ። እዚህም ብዙ ልጆች ትቶ ነው የሞተው ። የሱን እንትውና እዚያ ማዶ ደግሞ ትመለከታለህ?' አሉኝ ። ያ ያሳዩኝ ቦታ የራዲዮ መገናኛ ጣቢያቸው ነው ። ከአዲስ አበባ የመጣው ወጣቱ ኦፕሬተርም በየቀኑ ያለውን የወታደር ንቅናቄ ፤ ከፈረንሣይና ከኢጣሊያ ጋዜጦች የሚያገኘውን ሁሉ ለአፈወርቅ ይሰጣል ። መልእክትም ያስተላልፋል ።

"ያን ውብ የሆነ የጦር ካምፕ ጐብኝቻለሁ ። በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ ነው ። ለአየር ወረራ መከላከያ የሚሆነው ምሽግ ጠመዝማዛ እየሆነ ተበጅቷል ። የጠመንጃዎቹ ግምጃ ቤት ፤ ወታደሩን እየሰበሰቡ የሚያናግሩበት ቦታ ሁሉ በሚገባ የተዘጋጀ ነው። አንዱ ካሚዮናቸውና ሁለቱ ፈረሶቻቸው ዝግጁ ሆነው ሙላህ ካምፕ ውስጥ ቆመዋል ። ይህ ሁሉ ዝግጅት የተፈፀመው በሶስት ሳምንት ጊዜ ነው..." በማለት እስቲር አድናቆቱን ይገልፃል ።

እስቲር ጽሑፉን በመቀጠል እንዲህ ይላል "...ሁልጊዜ ፀሐይዋ ልትጠልቅ ስትል ወታደሩ ይሰለፍና አፈወርቅ ባሉበት የኢትዮጵያ ባንዲራ ከተሰቀለበት ይወርዳል ። አፈወርቅ የተለመደ ንግግራቸውን ያሰማሉ ። 'ኢጣሊያ ፤ ኢትዮጵያን ለመውረር ተነስታለች ። እኔ ሳልሞት ኢትዮጵያ አትወረርም ። ከሞትሁ በኋላ ግን የፈለገው ይሆናል ። የማውቀው ነገር አይኖርምና ያኔ ግድየለኝም' ይላሉ ። እኔም ብሆን በአፍሪካ ውስጥ ከዚህ ጠንካራ ሕዝብ መሀል ለመገኘት ያበቃኝን እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ ። ሲጨልም አፈወርቅ ከተቀመጡበት ቦታ እንጨት ይነድና አፈወርቅ ራታቸውን በልተው ቡና ይጠጣሉ ። አንድ ቀን አብረን ራት እንድንበላ ጋበዙኝ ። ወጣቱ መኰንን አሲ ኑር ከጠረጴዛዋ እግር ሥር ቁጭ ብሏል ። እንጀራ በወጥ ከበላን በኋላ ማንጐና ብርቱካን ቀረበልን ። ያን እየበላን ስንጫወት በመሀሉ አፈወርቅ ጨዋታውን ለወጥ አደረጉና 'ይሄ የሊግ—ኦፍ—ኔሽንና የእንግሊዝ ጉዳይ አልገባኝም ። ከራዲዮ እንደምሰማው በሽታ የሚያመጡ ናቸው ። ያሳምሙኛል ። እንቱንም ቢሆን ንጉሠ ነገሥቱ ጦሩን እንዳስጐበኝህ ስላዘዙኝ ነው ያሳየሁህ' ሲሉኝ ስለ እንግሊዝ ያለኝን አስተያየትና መልካምነት አጫወትኳቸው ። እሳቸውም 'ደህና ነው ፤ ይሆን ይሆናል ፤ በመሆኑም ይመስለኛል ዛሬ ማታ ንጉሠ ነገሥቱ ሁሉን ነገር እንዳሳይህ በቴሌግራም አዘውኛል' ብለው ተነሱ። ከኢጣሊያ የተማረኩ ጠመንጃዎችንና በሣጥን የተቀመጡ ጥይቶችን አሳዩኝና 'ይሄውልህ ፤ እነኚህ ከባንዳዎች የማረክናቸው ናቸው' ብለውኝ ልንወጣ ስንል አንድ የእንግሊዝ ጨው የተቀመጠበትን ሣጥን አሳዩኝና 'ለወታደሮቼ በጣም የሚጠቅማቸው ይሄ ነው' አሉኝ ።

"በካምፑ ውስጥ እየዞርን ስንጐበኝ 300 ወታደሮች ምሽግ ይዘው ሲጠባበቁ አየን ። ወታደሮቹ የያዙት መሣሪያ ዘመናዊ ነው ። መትረየስ ተኳሹ አቶ ወልደ ማርያም ተጠራና በተጠንቀቅ ያሉትን ሁለት መትረየሶችን እንዲተጠመዱ አሳየኝ ። አንድ ነገር ቢነሳ መትረየሶቹን እንዴት በቀላሉ እንስቶ ለማንዝና በቀላሉ ደግሞ ወራሪውን ለመቋቋም እንደሚቻል ካሳየኝ በኋላ አፈወርቅ ፤ና ደግሞ የኔን ሳሳይህ ብለው ወሰዱኝ ። የወሰዱኝ ፀረ አይሮፕላን የሆነው ኦርሊኮናቸው ከተጠመደበት

ቦታ ነው ። ከዚያም ደርሰን በጨረቃዋ ብርሃን ስንመለከት ‘ይሄውልህ፣ለአይሮፕላን መከላከያ የተሰጠን ይሄ አንዱ ብቻ ነው ። እሱንም የያዝኩት እኔ ነኝ ። ይሄን መሣሪያ የሸጡልን ሰዎች ግሩም መሣሪያ ነው ብለውናል ። ነገር ግን እነሱም አሮፓውያኖች ስለሆኑ ምናልባት አታለውን ይሆን ይሆናል ። እንደነገሩንማ ቀይ ላሳይህ’ ብለው ኦርሊኩን አዘቀዘቁና ‘እንዲህ ሆኖ ሲተኮስ ደግሞ ፀረ-ታንክ ይሆናል !’ እያሉ አሳዩኝ ። ከሁለት ወር በፊት በዚህ ኦርሊኮን አፈወርቅ በሃያ አይሮፕላኖች ላይ ተኩሰዋል ።

“ቆራሄ በየጊዜው በአይሮፕላን ቦምብ ይደበደባል ። ከሚወድቀው ቦምብ ቢለዋ እየሠሩ ስለሚጠቀሙበት አፈወርቅ ሥጋ የሚበሉት ከቦምብ ፍንጣሪ በተሠራ ቢለዋ ነው ።

“ከዚሁ ከሚወድቀው ቦምብ ውሃ መጠጫም ሠርተው ውሃ የሚጠጡት በቦምብ ኩባያ ነው ። ስለዚህ ነገር አፈወርቅ ሲያጫውቱኝ ‘ይሄ ፖምፕ ጨሽቱ ያደነቁረናል እንጂ መንካት አይነካንም ። እኛም እንዲህ፣እንዲህ እየሠራን እንጠቀምበታለን’ ብለውኛል ።...” ሲል እስቲር ጽፏል ።

ግራዝማች አፈወርቅ ቆራሄ ላይ ባሠሩት ምሽጋቸው ውስጥ ሆነው ከቦምብ በተሠራው ቢለዋ ሥጋ ይበላሉ ። ሥጋውን በልተው ፣ከቦምብ ዋንጫ የሚጐነጩትን ይጐነጫሉ ። እስቲር እንደጻፈው “...አፈወርቅ ዘንድ ከደረስኩበት ጊዜ ጀምሮ በቆራሄ ላይ ብዙ ምሽጎች ተቆፍረዋል ። ምሽጎቹ የተሠሩት ከሚወርድባቸው የቦምብ ድብደባ እንዲያስጥሉ ሆነው ነው ። በምሽጎቹም ውስጥ 1500 ኢትዮጵያውያን ወታደሮች አሉባቸው ። የአፈወርቅ ራዲዮ ከታፈረ ከተማና ከሐረር ጋር በየቀኑ ግንኙነት ያደርጋል ።

“መስከረም 24፣25 እና ጥቅምት 1 ቀን ኮፕሮኒስ የተባሉ ስድስት አይሮፕላኖች እየተመላለሱ የቆራሄን ምሽግ በቦምብ ደበደቡ ። ምሽጉ ግን እንደ እሌት ጠጥሮ ምንም አላስነካም ። አፈወርቅ ከፈረሰው ከሙላህ ግቢ ሆነው ኦርሊኩናቸውን ይተኩሳሉ ። ከአይሮፕላኖቹ የሚጣለው ቦምብ ዙርያውን ይወድቃል ።

“በተለይ መስከረም 25 ቀን ቆራሄ ላይ የተጣለው ቦምብ 300 ነበር ። አንድ መቶውን የቆጠሩት አፈወርቅ ናቸው ። እነኚህ አንድ መቶ ቦምቦች በአፈወርቅ ዙርያ ሲወድቁ አፈወርቅ ሳይደነግጡ ልበ ሙሉ ሆነው የቦምቦቹን ፍንዳታ ይቆጥሩ ነበር ። በዚያን ዕለት አምስት ሰዎች ሲሞቱ 15 ሰዎች ቆሰሉ ። ጥቅምት 1 ቀን በተደረገው ጦርነት የራዲዮ ኦፕሬተራቸው ከጥቂት ሰዎች ጋር ሸሽተው ሊያመልጡ ወጡ ። ያን የሸሸ ኦፕሬተር ወዲያው ይዘውት ሥራውን እንዲቀጥል አደረጉት ።

“ወደ ሙስታሂል ሲል ዋቢ ሸበሌ ወንዝ አጠገብ ያለው የታፈረ ከተማ ምሽግ በቦምብ ክፉኛ ተደበደበ ። በታፈረ ከተማና በቆራሄ መሀል ያለው የሸላቦ ምሽግ ጥቅምት 1 ቀን በቦምብ በኃይል ተመታ ። ኢትዮጵያውያን ወታደሮች አይሮፕላኖቹን ለመምታት በየምሽጋቸው ሆነው ይተኩሳሉ ። አፈወርቅ በወታደሩ መሀል እየተገኙ ያነቃቃሉ ። በራዲዮ መገናኛም ርዳታ እንዲደርስና ጦራቸው እንዲጠናከር ይጠይቃሉ ። ለጥያቄያቸው ሁሉ ግን መልስ አላገኙም ። የኢጣሊያ ብረት ለበስ የወታደር ክፍል ጥቅምት 4 ቀን ታፈረ ከተማን ለመያዝ ተንቀሳቀሰ ። ለዚያን ዕለት አጥቢያ በታፈረ ከተማና ቆራሄ ላይ ከባድ ዝናብ ሲዘንብ ስላደረ መካናይዝዱ ብርጌድ ሊንቀሳቀስ አልቻለም ። መሬቱ መኪናዎቹን ይውጣቸው ጀመር ። ዝናቡ ጥቅምት 5 ቀንም ቀጥሎ ዋለ ። ከዚህ በኋላ በአይሮፕላን ክለላ የሚታጀብ እግረኛ ጦር ተላከ ። እግረኛው የኢጣሊያ ጦር ታፈረ ከተማንና ሸላቦን አጠቃ ። ሙስታሂልና ፈርፈር ያሉትንም ምሽጎች ያዘ ። በእነኚህ ምሽጎች ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን በርትተው ተዋግተዋል ። ከሁለቱም በኩል ከባድ ጉዳት ደርሷል ።

"ታፈረ ከተማ ላይ ዝቅ ብለው በማንዣበብ ኢትዮጵያ ወታደር ላይ መትረየስ ከሚተኩሱት አይሮፕላኖች መሀል ሁለቱ አይሮፕላኖች ተመትተው መውደቃቸውን አፈወርቅ ሰሙ ። ከዚህ በኋላ አይሮፕላኖቹ ከ3000 ሜትር በላይ እንጂ ከዚያ በታች ለመብረር አልቻሉም ።

"ቆራሄን አልፎ ያለው የቀብሪደሐር ምሽግ በቦምብ ክፉኛ ተደበደበ ። ገርለጉቢ ፣ ታፈረ ከተማና ሽላቦ ተያዙ ። የአፈወርቅ ሰላዮችም መጥተው ግራናሌ ያለው የውሃ ጉድጓድ መያዙን ነገሩዋቸው ።" በማለት በጦሩ ሜዳ የነበረውን እስቲር ይተነትናል ።

ከጦርነቱ በኋላ ኢጣሊያኖቹ ራሳቸው እንደጻፉት አፈወርቅ ቆራሄ ላይ በርከት ያሉ ፀረ ታንክ መሣሪያዎችና 60 መትረየሶች ነበሩዋቸው ብለዋል ። ለኢጣሊያኖቹ ብዙ መስሎ የታያቸው የአፈወርቅ አትኳኮስ ነው እንጂ አፈወርቅ ያለአንድ ኦርሊኮን አልነበራቸውም ። መትረየሶቻቸውም አራት ብቻ ሲሆኑ ያሏቸው አውቶማቲክ ጠመንጃዎች አርባ ያህል ነበሩ ።

አስቸጋሪ ሆኖ የቆየውን የቆራሄን ምሽግ ኢጣሊያኖች በተጠናከረ ኃይል ለመስበርና ለመያዝ ተነሱ። ስድስት ክፍለ ጦር ወታደሮች ተዘጋጁ። 150 ከሚዮኖች፣ አራት ታላላቅ መድፎች ፣ ዘጠኝ ታንኮችና 30 ብረት ለበስ መኪናዎች ባንድነት ሆነው በፌርፌር መንገድ መግባት ጀመሩ ። ስንቁ ፣ ትጥቁ የተሟላለት የኢጣሊያ ጦር ወደቆራሄ በሚያመራበት ጊዜ ቆራሄ ያለው የኢትዮጵያ ጦር የነበረው ጭብጥ በሶና የመጨረሻዋ ኩባያ የማትሞላ ውሃ ብቻ ነበረች ።

ቆራሄ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ረዳት በማጣት ዙርያውን ስለተከበበ እንኳን ጥይት ፣ ስንቅ ማቀበያ ቀዳዳ የለም ። የውሃዎቹ ጉድጓዶች በጠላት እጅ ተይዘዋል ። በየቀኑ በአይሮፕላን ቦምብ ይደበደባል ። በአጋዴን ምድር በቆራሄ የነበረው የኢትዮጵያ ወታደር ግን ችግሩን ችሎ ይዋጋል እንጂ ችግር አሸንፎት እጁን ለጠላቱ አልሰጠም ። ይህን ሁሉ ያደረገ የአፈወርቅ ንግግር ነው ። አፈወርቅ በየወታደሩ መሀል እየዞሩ "አብረን እንደበላን አብረን እንሙት እንጂ እኔን ጥለህ የት ትሄዳለህ ? በሰላሙ ቀን ከወደድከኝ ፣ በዚች ቀውጢ ቀን ብቻዬን ትተህ እንደማትሄድ አውቃለሁ ። እንደምትወዱኝ አወዳችኋለሁ ። በሰላሙ ጊዜ ጭብጥ በሶ ተካፍለን አብረን በልተን አሁን እንዴት ይርበናል? ስንቄን አካፍዬ እንዳበላሁህ የመከራዬም ተካፋይ ሁነኝ ። አፈወርቅ እጁን ለጠላት አይሰጥም ። አንተም የአፈወርቅ ነህና የተቀደሰ እጅህን ላልተቀደሰ ጠላት አትስጥም" እያሉ የተለመዱ ንግግራቸውን በየቀኑ ያሰሙታል ። ለዚህ ነው የቆራሄ ጀግኖች ለጠላት ከፍተኛ ጦር አልበገር ያሉት ።

አፈወርቅ ጥሩ ጥሩ የሶማሌ ሰላዮች ነበሩዋቸው ። ስድስት ባታሊዮን ጦር ወደቆራሄ ለመምጣት መዘጋጀቱን ቀደም ብለው ነግረዋቸዋል ። አፈወርቅም ዝግጅት ጀመሩ ። በነሐሴ ወር ከሐረር የመጡትን 500 ወታደሮች ከቆራሄ በስተምሥራቅ ባለው ደን ውስጥ አስለፏቸው ። እነኚህም 500 ወታደሮች በየዱሩ ተሸሽገው የጠላት ጦር ሲመጣ እንዲቆርጡት አዘዙ ። ለወታደሮቹም ቆራሄ ላይ ከተረፈቻቸው ስንቅ ሰጥተው ውሃም በየቅላቸው አስይዘው ላኩዋቸው ።

እስቲር እንደጻፈው "...ጥቅምት 23 ቀን ሃያ አይሮፕላኖች መጥተው ቆራሄን ክፉኛ በቦምብ ደበደቡ ። አይሮፕላኖቹ ባንዱ ብቻ ሳያበቁ እየተመላለሱ እጅግ በጣም ብዙ ቦምብ ጣሉ ። አይሮፕላኖቹ የተጫኑትን ቦምብ ቆራሄ ላይ ጥለው እንደገና ጭነው ለመመለስ የሚወስድባቸው ጊዜ እኩል ሰዓት ብቻ ነው" ብሏል ።

አፈወርቅ ኦርሊኮናቸውን ይተኩሳሉ ። በየአቅጣጫው ወደሚመጣው አይሮፕላን ኦርሊኮናቸውን እያዘቀወሩ ይተኩሳሉ ። በሚተኩሱበት ጊዜ በቦምብ እግራቸውን ተመቱ ። እዚህ ላይ እስቲር ሲገልጽ "ቁስሉ ከባድ ነበር ። አፈወርቅ ግን እሳ

ባቸው ስለቁስላቸው ሳይሆን ስለቆራኄ ነበር ። 220 ኪሎ ሜትር ከሚርቀው ከደገሕቡር የቀይ መስቀል የሕክምና ቡድን አለ ። አፈወርቅ ይህን ያውቃሉ ። ግን አፈወርቅ ቁስላቸውን ለመታከም ወደዚያ ቢሄዱ ወታደሩ ሁሉ እንደሚከተላቸው ስለሚያውቁ እምቢ አሉ ።

"አጠገባቸው ያሉ ወታደሮች 'እንግዲያው ምሽግ ውስጥ አግብተን ከዚያ ይተኙ' ቢሏቸው 'እሰዋለሁ ፤ እንዲህ ያለውንም ነገር አላደርገውም ። ከዚሁ ሆኜ እታከሳለሁ' ብለው መለሱ ። ወደ ጦሩ አዛዥ ወደ ነሲቡም መልእክተኛ ልከው ከፋኛ መቁሰላቸውንና ቆራሔን ግን ሳይሞቱ እንደማይለቁ አስታወቁ ። ቢቻል እርዳታ እንዲመጣም ጠየቁ ።

"የአፈወርቅን መቁሰል የሚያውቁ ጀግናው የወላይታው ተወላጅ አሊ ኑር ፤ ፊታውራሪ ሰሙና የቤት አሽከሮቻቸው ብቻ ነበሩ ። አፈወርቅ ከፋኛ የቆሰለ እግራቸውን እየጐተቱ ኦርሊከናቸውን መተኮስ ጀመሩ ። ለጥቂት ጊዜ በኦርሊከኑ ድምጽ መጥፋት እንደመሰጋት ብሎ የነበረው የኢትዮጵያ ወታደር የኦርሊከኑን ድምጽ ሲሰማ የአፈወርቅ መኖርና ደህና መሆን ታውቆ ወታደሩ በያለበት ጠነከረ ።


"ጥቅምት 24 ቀን እንደገና 20 አይሮፕላኖች እየተመላለሱ ቆራሄን በቦምብ ይደበድቡ ጀመር ። አፈወርቅ የቆሰለ እግራቸውን እየጐተቱ ኦርሊከናቸውን ይተኩሱ ። የኦርሊከኑ ተኩስ እንደሌላው ቀን አልነበረም ። ከፋኛ ቆስሎ ያደረው እግራቸው ከፋኛ በላመማቸው የኦርሊከኑ ድምጽ የሚሰማው ዘግየት እያለ ነው ። ኦርሊከኑን እንደፈለጉ ለማዘዋወር ባለመቻላቸውም ባለበት አቅጣጫ ኢላማ እስኪገባ ይጠብቃሉ ። ቀኑን ሙሉ በቦምብ ሲደበድቡ ውለው የአይሮፕላኖቹን መመላለስ ምሽት ገታው ።

"ነጋ ፤ ጥቅምት 25 ቀን እንደገና ሃያዎቹ አይሮፕላኖች እየተመላለሱ የቦምብ ድብደባቸውን ጀመሩ ። ጀግናው አፈወርቅ ከተኛበት እየተንፏቀቁ ያን የቆሰለ እግሩን እየጐተተ ኦርሊከኑ ዘንድ ደረሰ ። በዚህ ቀን የነበረው የቦምብ አወራረድ ከሌላው ቀን ሁሉ የተለየ ነበር ። ጆሮ ፤ ሌላ ምንም ነገር መስማት አልቻለም ነበር ። መሬቲቱ ተንቀረቀበች ። ከሚነሳው አቧራ ብዛት የተነሳ አንድ ወታደር ከፊቱ ምን ነገር እንዳለ ማየት አይችልም ነበር ። መሬቷ ላይ የሚታይ ነገር ቢኖር እሳት ብቻ ነው ። በሙሉ ተንቀለቀለ ። በአየር ላይ የሚፈነዳው ቦምብም ነጐድጓድ መሰለ ። መሬቲቷ ከእሳቱ ብዛት የተነሣ ቢጫ መሰለች ። የሚሰማው ድምፅም ተራራ የተናደና የወደቀ ይመስላል" በማለት እስቴር በሥፍራው ሆኖ ያየውን ይመሰክራል ።

እስቴር ስለመጨረሻዋ ሰዓት ሲጽፍ "የአፈወርቅ ኦርሊከን ዝም አላለም ። አፈወርቅ ጥቂት ቆይቶ ደከመ ። ኦርሊከኑ ላይም ድፍት አለ ። እጆቹ ዝለው መሬት ላይ ወደቁ ። አፈወርቅ ከተመታ ጀምሮ ከቁስሉ ደም ይወርድ ነበር ። አፈወርቅ ኦርሊከኑ ላይ ድፍት ብሎ የዛሉት እጆቹ መሬት ሲነኩ የአፈወርቅ የቁስሉ ደም ቆመ" በማለት ስለወጣቱ ጀግና ስለግራዝማች አፈወርቅ አሟሟት ይተርካል ።



ገርለጉቢ የኢፈወርቅ ጦር ሰፈር ።




የአፈወርቅ ቃፊር የአይሮፕላን መምጣት ሲጠብቅ ።



በኢጣሊያ ጦር አይሮፕላን ፎቶግራፍ የተነሳው የቆራሄው የአፈወርቅ ጦር ሠፈር ።




የቆራሄው ሠፈር በቦምብ እየተደበደበ ሲቃጠል ።



ምሽግ ውስጥ ያለችው የአፈወርቅ ቤት ።



የመጨረሻዎቹ ሰዎች በቆራሄ ምሽግ ።



የቆራሄው መታከሻ ።

# በሊግ ኦፍ ኔሽንስ የተደረገ ክርክር

የኢጣሊያ ሠራዊት ወሰን አልፎ እፍዱብ ድረስ መያዙንና ወደ አዶና ወደ ገርለጉቢ መንገድ መሥራት መጀመሩን ጭምር ኢትዮጵያ ታህሳስ 15 ቀን 1927 ዓም ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ አመለከተች ። ኢጣሊያም ከቅኝ ግዛቱ ወሰን ያለማለፉንና ከግዛቱም ያለመውጣቱን ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ በሰጠው መልስ አረጋገጠ ። ኢጣሊያ እንደ እውነተኛ ፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀሰተኛ ተቆጥረው ኢጣሊያን በመፍራት ብቻ ክርክሩ ቆመ ። በዚያን ጊዜ የፈረንሣይ ጊዜያዊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሙሴ ረኔ ለእንግሊዙ ለሚስተር ኤደን ይህንን ጉዳይ አንስተው ሲያጫውቱ "... ይሄ የአበሾች ጥያቄ እንደማንቹሪያ ጉዳይ መጥፎ መጥፎ ጠረን ይሸተኛል... አሉ" ሲል አቮምን ጽፎታል ።

ኢጣሊያ ወሰን እየገፋ ሄደ ። ገርጉቢ ደረሰ ። ይህንኑ ገርጉቢ መድረሱን የኢትዮጵያ መንግሥት ታህሳስ 25 ቀን 1927 ዓም ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ አመልክቶ ከወሰን መግፋቱ እንዲታገድ ሲል ፍርድ ጠየቀ ። በዚህ ጊዜ በሊጉ ስብሰባ የእንግሊዝ መንግሥት ተወካዮች የሆኑት ሰር ጆን ሲሞን እና ሰር አንቶኒ ኤደን ፤ የፈረንሣይ መንግሥት ተወካይ የሆኑት ላቫል ባንድነት ሆነው የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካይ የሆኑትን በጅሮንድ ተክለሐዋርያትን በአሳብም ሆነ በሞራል ድጋፍ ተጫኑዋቸው። ጉዳዩም ለጥር 9 ቀን ተቀጠረ ።

ጥር 9 ቀን የተሰበሰበው ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ኢጣሊያን በመፍራት ብቻ እውነተኛ ፍርድ መፍረድ አቅቶት ጉዳዩን ለመጉተት ሲል በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሀል ያለው ጉዳይ አጀንዳ እንዲይዝ በማለት ወሰነ ። የኢጣሊያ መንግሥት ተወካይም "ይህ ነገር በሁለቱ መንግሥታት ስምምነት በሰላም የሚያልቅ እንጂ ይህን ማኅበር ሊግ ኦፍ ኔሽንስን አያገባውም ። ምክንያቱም ጉዳዩን የሁለቱ አገሮች ተካላዮች በስምምነት የሚወስኑት ስለሆነ በአጀንዳ መያዝ የለበትም" ሲል አመለከተ ። የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካይም "ጉዳዩ በሰላም የሚያልቅ ከሆነ ይህን አሳብ እንቀበላለን" አሉ ።

ኢጣሊያ በሰበብ አስባብ ጉዳዩን ከሊግ ኦፍ ኔሽንስ አጀንዳ ካወጣ በኋላ ሰላማዊ ንግግር መጀመር ቀርቶ ጦሩን በቅኝ ግዛቶቹ ማከማቸት ጀመረ ። የኢትዮጵያ መንግሥትም እንደገና "....የኢጣሊያ መንግሥት በሶማሊያና በኤርትራ ጦር ማከማቸት ላይ ነው ፣ ...ከዚህ በፊት ጉዳዩን በሰላም እንጨርሳለን በማለት ለዚህ ጉባዔ ቃል በገባው መሠረት ለመፈፀም አሻፈረኝ ብሏል ..." በማለት ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ መጋቢት 8 ቀን አመለከተ ።

መጋቢት 13 ቀን የተሰበሰበው ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ጉባዔም "...ሁለቱ መንግሥታት ማለት ኢጣሊያና ኢትዮጵያ ወሰን የሚያካልላቸው ሌላ 3ኛ ዳኛ በ30 ቀናት ውስጥ በስምምነት መርጠው ለጉባዔው እንዲያቀርቡ ፤ ባያቀርቡ ጉባዔው ተጨማሪውን 3ኛ ዳኛ ይመርጣል..." ሲል ወስኖ ተበተነ ።

ጉባዔው ስለሶስተኛው ዳኛ ወስኖ ከተበተነ ከ15 ቀናት በኋላ የኢጣሊያ መንግሥት ሚያዝያ 2 ቀን ለሊጉ ዋና ፀሐፊ ባቀረበው ማመልከቻ "... እኛ በሰላም መንገድ በዲፕሎማቲክ በኩል ጉዳዩን ለመጨረስ ስንችል ፣ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ዳኛ መርጣችሁ አቅርቡ ያለን ያለአግባብ ስለሆነ ውሳኔው ይነሳልን..." ሲል አመለከተ ። ሚያዝያ 7 ቀን የተሰበሰበው የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ጉባዔ በፈረንሣይና በጀርመን መሀል

ስላለው ጉዳይ ተነጋግሮ ሲጨርስ የሊጉ ፀሐፊ የኢትዮጵያንና የኢጣሊያን ጭቅጭቅ አቀረቡ ። የሁለቱም መንግሥታት ማለት የኢትዮጵያና የኢጣሊያ መልእክተኞች በጉባዔው ላይ የየበኩላቸውን አቤቱታ አቀረቡ ። በመጨረሻ የጉባዔው ፕሬዚዳንት "...ሁለቱ መንግሥታት ዳኛ መርጠው ነገሩን በሰላም እንዲጨርሱ ወስነናል ። በመሀላቸው ያለው ጉዳይም ይሄን ያህል አስጨናቂ አይደለም ። እንነጋገርበትም ከተ ባለ ለግንቦት ወር አጀንዳ ይያዝላቸው..." በማለታቸው ለግንቦት 17 ቀን አጀንዳ ተያዘለት ።

የቀጠሮው ቀን እስቲደርስ ድረስ የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት ፔር ላቫል ከኢጣሊያ ጋር ሮም ውስጥ የተለየ የወዳጅነት ውል ተፈራረሙ ። በቀጠሮው መሠረት ግንቦት 17 ቀን የተሰበሰበው የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ጉባዔም "...በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መሀል ያለው ክርክር በወሰን አካላይ ዳኛ የሚያልቅ ስለሆነ ወሰናቸውን በዳኛ ይካለሉ ። ኢጣሊያ የጦር ኃይልዋን በቅኝ ግዛቶችዋ ታከማቻለች የተባለው ግን በማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ ስለሆነና ቢቀርብም ደግሞ አንድ መንግሥት በግዛቱ ጦር እንዳያስቀምጥ የሚከለክል ሕግ ስለሌለ የኢትዮጵያን መንግሥት አቤ ቱታ አልተቀበልነውም። ...በዚህ መሠረት ለወሰን አካላይነት የሚመረጡት ዳኞች ሥራቸውን ይቀጥሉ ። ሪፖርታቸውንም ለመስማት ጉዳዩ ለጁላይ 25 ተቀጥሯል ።...." በማለት ወሰነ ።

የኢጣሊያ መንግሥት ለወሰን ተካላይነት በበርሊን የኢጣሊያ አምባሳደር የሆነውን ኮንት ሉዊጂ አልድሮቫንዲ (Aldrovandi) እና ሩፋኤል ሞንታኛ እን ዲሆኑ መረጠ ። ኢትዮጵያም በኢንተርናሽናል ሕግ አዋቂነት የታወቁትና በፓሪስ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፕሮፌሰር የሆኑት ፕሮፌሰር ጂኦፍሬ እና በኢንተርናሽናል ሕግ በኒውጀርሲ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ፒትማን ፖተር ዳኛ እንዲሆኑላት መረጠች። ሙሶሊኒ ይህን የኢትዮጵያን ምርጫ በመቃወም ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ በጻፈው ደብዳቤ "....የኢጣሊያ መንግሥት እንዳደረገው ሁሉ የኢትዮጵያም መንግሥት ዳኞቹን መርጦ ማቅረብ ያለበት ከኢትዮጵያውያን እንጂ ከውጭ አገር ሰው መሆን የለበ ትም...." አለ ። ተቀባይ ግን አላገኘም ።

የእነዚህ የተመረጡት ዳኞች ጉባዔ ግንቦት 29 ቀን ሚላን ውስጥ ተሰበሰበ ። ጉባኤው ለጉባዔው ጸሐፊነት አራት ሰዎች እንዲመረጡ ወስኖ ሶስቱ ኢጣሊያውያን ማለት በኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር የሆኑት ኢንሪኮ ቼሩሊ ፤ በኢጣሊያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲሬክተር የሆኑት ጓርናስኬሊ (Guarnaschelli) እና ካፒቴን ዛንኪ (Zanchi) ሲመረጡ ሌላው አራተኛ ፀሐፊ ኢትዮጵያ ለዳኝነት የመረጠቻቸው የጆፍሬ ልጅ ሬይሞንድ ነበር ። ጉባኤውም ሌላ ሥራ ሳይሠራ ይቺው ሥራ ሆና በዚችው ምርጫ ብቻ የሚቀጥለው ስብሰባ ጁን 25 ቀን ሆላንድ ውስጥ እንዲሆን ወስኖ ተበተነ ።

ጁን 25 ማለት ሰኔ 18 ቀን ሆላንድ ውስጥ በተደረገው ስብሰባ ከኢጣሊያ በኩል ፕሮፌሰር ሊሶና እና ሌሎችም የኢጣሊያ መኳንንት የኢጣሊያን መንግሥት ወክለው ፤ በኢትዮጵያም በኩል የፓሪስ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ፕሮፌሰር ጋስቶን ዠዜ (Jeze) እና በፓሪስ የኢትዮጵያ መንግሥት ሚኒስትር የነበሩት በጅሮንድ ተክለሐዋርያት የኢትዮጵያን መንግሥት ወክለው ተሰበሰቡ ። ስብሰባው ከየመንግሥታቱ ተወካዮች ጋር ከተዋወቀ በኋላ ሌላ ፋይዳ ያለው ሥራ ሳይሠራ ለሰኔ 27 ቀን ተቀጥሮ ተነሳ ።

ሰኔ 27 ቀን በተደረገው የወሰን አካላይ ዳኞች ጉባዔ ፕሮፌሰር ሌሶና የኢጣ ሊያ መንግሥትን አሳብ አመለከቱ ። ንግግራቸውም ያው የተለመደው ወሰን አላለፍ ንም ፤ በሰላም እንካለል የሚለው ነበር ። የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካይ የሆኑት ፕሮፌሰር ዠዜ ደግሞ ጠቅላላውን ሁኔታ አመልክተው የወልወልን ግጭት በማስረጃ

እየደገፉ አስረዱ ። ዳኞቹም በፕሮፌሰር ዠዜ ንግግር ተመርጠው እውነተኛውን ፍርድ ለመፍረድና የኢጣሊያን ወሰን ገፊነት አውቀው ውሳኔ ሊያሳልፉ ሲሉ ፕሮ ፌሰር ሉሰና ተንስተው "....በዚህ ጉዳይ መነጋገር የለብንም ...." በማለት አመለከቱ። ከኢጣሊያ በኩል የተመረጡት ሁለቱ ዳኞች "የሉሰና አሳብ ልክ ነው ፤ መነጋገር የለ ብንም" ሲሉ በኢትዮጵያ በኩል የተመረጡት ዳኞች ደግሞ "የኢትዮጵያ መንግሥት በማስረጃ የተደገፈ አቤቱታ ስላቀረበልን በማስረጃው መሠረት መነጋገር አለብን" ሲሉ ተከራከሩ ። በዚህ ጭቅጭቅ ብቻ ጊዜው አልፎ ጉባዔው ተዘጋ ።

የሁለቱ መንግሥታት ክርክር የሚወስነው ወሳኝ አጥቶ ጉዳዩ ወደተጀመረበት ወደ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ተመለሰ ። ሐምሌ 24 ቀን የተሰበሰበው ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ጉባዔ "አንድ ሌላ 5ኛ ዳኛ ይጨመርና የሱ ቃል ወሳኝ (ቬቶ) ይሁን" አለ ። የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካይ ፕሮፌሰር ዠዜ ጉዳዩ ምንም የማያከራክርና ወልወል የኢትዮ ጵያ ግዛት መሆኑን በበቂ ማስረጃ አስደግፈው አመለከቱ ። የኢጣሊያ ማንገዋበብ ወጥሮ የያዛቸው የጉባዔው ዳኞችም የኢትዮጵያን መንግሥት አቤቱታ ሳይቀበሉ "የሁለቱ አገሮች ችግር ተጠንቶ ለሴቴምበር 4 ይቅረብልን" በማለት በድፍን ጉባዔውን ዘግተው ተነሱ ።

ሴቴምበር 4 ወይም ነሐሴ 29 ቀን የተሰበሰበው የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ጉባዔም "....በወልወል የተነሳው ግጭት አጋጣሚና ያልታሰበበት ድንገተኛ ነው ። ይህም መሆኑን ሁለቱም መንግሥታት አምነዋል ። የኢትዮጵያ መንግሥት ወልወል ግዛቴ ነው ሲል የኢጣሊያ መንግሥትም ወልወል የኔ ግዛት ነው ብሏል ። በቦታው ላይ የተጣለው ቦምብና የደረሰውም እልቂት ቢሆን በኢንተርናሽናል ደረጃ ሲታይ ይሄን ያህልም አስደናቂ አይደለም ።...." ብለው መላ የሌለው የፍራቻ ውሳኔ ወሰኑ ። የኢትዮጵያን የክስ አቤቱታ ማየት የጀመረው የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ጉባኤ አለቀ ። የኢጣሊያም ጦር ክምችት ተጠናቀቀ ። በጥቅምት ወር 1928 ዓም ኢጣሊያ በየአቅ ጣጫው ጦር ከፍታ ወሰን እያለፈች አገር መያዝ ጀመረች ።

—O—



በጀርጎድ ተክለሐዋርያት ከመሀል ካሉት ከሙሴ ዠዝ እና ከሙሴ ላቫል ጋር ሲመካከሩ ።




በጅሮንድ ተክለሐዋርያት ከመሀል ካሉት ከሙሴ ዠዝ እና ከሙሴ ላቫል ጋር ሲመካከሩ ።



በጅሮንድ ተክለሐዋርያት ከጉባኤው አዳራሽ ሲገቡ ።



የኢትዮጵያንና የኢጣሊያን ጉዳይ የሚመለከተው ጉባኤ ።



ግሪካዊው ፖለቲስ ጉባኤውን ሲመሩ ።

# የኢጣሊያ ጦር ዝግጅት

"በቅኝ ግዛት ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው ታላቅ ጦርነት ነው"

ቪቶሪዮ አማኑኤል የኢጣሊያ ንጉሥ

Con l'Etiopia Abbiamo Pazientato Quarant' Anni: Ora Basta.

ኢትዮጵያን ለ40 ዓመታት ታገስን ። አሁን በቃ ።

ሙሶሊኒ

ጥቅምት 3/1935 (እ.ኤ.አ.)

ሙሶሊኒ በ1926 ዓም የቅኝ ግዛቱን ሊቢያን ጐብኝቶ ነበር ። ሊቢያን እየተዘዋወረ ከጐበኘ በኋላ ወደ ሮማ ለመሔድ ከዋናዋ ከተማ ከትሪፖሊ ሲነሳ ለተሰበሰበው የኢጣሊያ ሠራዊት ንግግር ሲያደርግ "...ሶማሊያን ጐብኝቻለሁ ። ይሄው አሁን ደግሞ ሊቢያን ጐበኘሁ ። ሁለቱም አሽዋ የተሞሉ ሳጥኖች ናቸው ። ወደ ኢትዮጵያ ግፉ ።..." ማለቱን ቤትሪስ የተባለ ደራሲ ዋት ኔክስት ፤ አ ዱቼ በተባለው መጽሐፉ ገልጾታል ። ከዚህ ንግግሩ ቀደም ብሎ በመስከረም ወር ዲስኩር ሲያደርግ "...የኢጣሊያ መመሪያ መቶ ዓመት በግ ሆኖ ከመኖር አንድ ቀን አንበሳ መሆን ይመረጣል የሚለውን ፍልስፍና መከተል ነው...." ብሎ ነበር ።

ዱቼ ሙሶሊኒ ከሁለቱም ዲስኩሮቹ በፊት በነሐሴ ወር ብቻ አምሳ ታላላቅ የኢጣሊያ የወታደር መርከቦች በስዊዝ ካናል በኩል ወደ ምሥራቅ አፍሪካ አልፈዋል ። የኢጣሊያ መንግሥት ወታደሮቹንና የጦር መሣሪያውን በስዊዝ ካናል በኩል ሲያሳልፍ 250,000 የእንግሊዝ ፓውንድ ለካናሉ ኪራይ ከፍሏል ። የኢጣሊያ ጦር ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ማለት ያን ጊዜ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ወደ ነበሩት ወደ ኤርትራና ወደሶማሌ የተጓዘው ሰባት ወር ሙሉ ነው ።

ጠቅላላ የጦሩ ዝግጅትና ክምችት ተጠናቆ ያለቀው በነሐሴ ወር ነው ። በኤርትራና በሶማሌ የሚከማቸው ጦር ተዘጋጅቶ ካለቀ በኋላ 250,000 የሚሆኑ የኢጣሊያ ወታደሮች "ሂዱ" የሚለውን ትእዛዝ ብቻ ይጠባበቃሉ ። ዝግጅቱ በጦር መሣሪያና በወታደር በኩል ብቻ ሳይሆን የወታደሩ ስንቅና ቁስለኛው የሚታከምበት የመርከብ ላይ ሆስፒታሎች ሁሉ ተዘጋጅተዋል ። ሙሉ የሆስፒታል ድርጅት ያላቸው መርከቦች ስምንት ሲሆኑ በእነኚህም መርከቦች ውስጥ 6000 ያህል አልጋዎች ተዘርግተውባቸዋል ። የእነኚህም መርከቦች ስም ኡራንያ ፤ ቴቬራ ፤ ካሊፎርኒያ ፤ ቪዬና ፤ ሄለን ፤ ቼሳሬ ፤ አኩሊያ ፤ ግራዲስ ይባላሉ ።

ዱቼ ሙሶሊኒ ቀደም ብሎ እ.ኤ.አ. መጋቢት 8 ቀን 1935 ዓም ለምሥራቅ አፍሪካው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ለጄኔራል ደቦኖ በጻፉላቸው ደብዳቤ ላይ "...ጦርነቱ በጥቅምት መጨረሻ ወይም በሕዳር ወር እንዲጀመር ይሁን ። ...ከሁለቱ ቅኝ ግዛቶቻችን ከተጨመሩት አንድ መቶ ሺ ጥቁር ወታደሮች ጋር አሁን 300 000 ወታደር አለህ ። በተጨማሪ 500 ያህል አይሮፕላኖችና 300 መኪናዎችም አሉህ ። ...በጥቅምት ወር ሶስት ዲቪዚዮን ጦር እንዲጨመርልህ ጠይቀሃል ። አስር እልክልሃለሁ ። እደግመዋለሁ ፤ አስር እልክልሃለሁ ። አምስት ዲቪዚዎን ከመደበኛው ወታደር ፤ አምስት ዲቪዚዮን ደግሞ በፈቃደኛነት ከሚዘምቱ ባለጥቁር ሸሚዞች እልክልሃለሁ ። እነኚህም የምልክልህ በጥንቃቄ የተመረጡና የሰለጠኑ ናቸው ።... በጥቂት ሺ ሰዎች እጥረት ምክንያት የአድዋን ድል አጣነው ። ያን ስህተት ዛሬ እንደግመውም ።...." የሚል ቃል ላከለት ።

ሙሶሊኒና ደቦኖ ይህን ደብዳቤ በተጻጻፉበት ጊዜ ኢጣሊያ በሁለቱ ቅኝ ግዛ ቶችዋ ያሠፈረችው ጦር ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች አገሮችም ማስገበሪያ ጭምር በቂ ነው ተብሎ ተገምቷል ። በዚያን ጊዜም 298 821 ወታደር ፤ 19 233 የጭነት እንስሳት ፤ 5 000 መኪናና ሞተር ብስክሌት ፤ 207 219 ቶን የሚመዝን የጦር መሣሪያ ፤ 26 000 መንገድ የሚሠሩ ተራ ኢጣሊያኖች በሁለቱ ቅኝ ግዛቶቿ ውስጥ ነበሩዋት ። ሙሶሊኒ በደብዳቤያቸው ለጀኔራል ደቦኖ ቃል በገቡላቸው መሠ ረት ጦርነቱ ሲጀመር ሲል የጦሩ ዝግጅት ብዛት 360 000 ወታደር ፤ 30,000 እን ስሳት (በቅሎና ፈረስ) ፥ 6500 መኪናና ሞተር ሳይክል ፤ ሶስት ሚሊዮን ቶን የሚመዝን የጦር መሣሪያና 50 000 መንገድ ሠሪ ተከማቸ ።

ኢጣሊያ የተዘጋጀችው በጦር መሣሪያ ብቻ አልነበረም ። ሰላዮችዋ ባቀረቡላት የኢትዮጵያ ሁኔታም ጭምር ነበር ። በተለይ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ አስጠንተው ለዶቦኖ የሰጡት የኢትዮጵያ ካርታ ጥሩ መመሪያና ጠቃሚ ሆንዋል ። ሌሎቹም ሰላዮች ቀደም ብለው በመግባት የመሄጃ መንገዱንና የማጥቂያ ቦታውን ሁሉ አጥንተው አቅርበዋል ። ጠቃሚ ጥናት ካቀረቡት ሰላዮችም መሀል ቱሊዮ ፓስቶሪ ይገኝበታል። ቱልዩ ፓስቶሪ በስለላ ተግባሩ ምን እንደሠራ ለአንጀሎ ዴል ቦካ አጫውቶት አን ጀሎ በመጽሐፉ ጽፎታል ። እንዲህ ይላል "…. ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ዓመታት የቆ የሁ ነኝ ። 64 ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ተዘዋውሬአለሁ ። ከንጉሥ ምኒልክ ጋርም ወዳጅ ነበርን ።…በ1924 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በኋላ ጀኔራል የሆነው ካፒቴን ማላድራ (Malladra) ጠራኝና አንድ ሚሽን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ስላሰብን አብረህ ለመሔድ ፈቃደኛ ነህን? አለኝ ።….ጂኦሎጂስት ነኝና በኢትዮጵያ ውስጥ በማ ዕድን ፍለጋ ስም ገብተን የኢጣሊያን ጦር በጉዞው ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን የመንገድ መሰናክሎች ማለት ወንዞችና ተራራዎችን እንድናጠና ነበር ።… ወንዞች በበጋና በክረምት ያላቸውን የውሃ ብዛት ሁሉ በሚገባ እየለካሁ እንዳጠናና ውሃ የሚበዛባቸውንም ወንዞች በየት በኩል ማቋረጥ እንደሚቻል የመሸጋገሪያውን መልካ ሁሉ እንዳጠና ነበር ።… ዝግጅታችን ካለቀ በኋላ በ1928 ዓም (እ.ኤ.አ.) ከእንግሊዛዊው ጂኦሎጂስት ኔስቢት (L.M. Nesbitt) ጋር ሆነን ከአዲስ አበባ እስከ ደንከል በረሃ እስከ ዳሎል ድረስ አጠናን ። ….በተለይ ከአዲስ አበባ ጂቡቲ የሚወስደው የባቡር ሀዲድ የሚያልፍበትን የአዋሽን ድልድይ ደህና አድርጌ አጠና ሁት ። የድልድዩን ደካማ ጐኑንም አጠናሁ ። አስፈላጊ ከሆነ ድልድዩን በፈንጂ ለማፍረስ የሚቻልበትን ሁሉ አጠናሁ ። ይህን በምንሠራበት ጊዜ በጉዞአችን ላይ ለሚያጋጥሙን መኳንንቶች ሁሉ በንጉሡ ላይ አድማ አድርገው እንዲነሱም እን ሰብክ ነበር ።…. አሁን አንዳንድ ሰዎች ደጃች ኃይለሥላሴ ጉግሣን ያስከዳው ባሮን ፍራን ኬቲ ነው ይላሉ ። እሱ አይደለም ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን ያስከዱት የሚስጢር ሠራ ተኞቻችን ሰርጀንት ኢሬ እና ሲኞር ሜአ ናቸው ።….በዚህ ስብከታችን ምክንያት ጦርነቱ በተጀመረ ጊዜ ከኢትዮጵያ ጦር ሶስት እጁ ያህል ሳይዋጋ ቀረ ። ለምሳሌ እንደ ደጃች አያሌው ብሩ ያሉት ጦራችንን በደስታ ተቀብለው የሸኙ ሰው ናቸው ። በዚህ በኩል የፖለቲካ ሰዎቻችን መልካም ውጤት አስገኝተዋል…."

የኤርትራ ገዥ የነበረው ኮራዶ ዞሊ "…በኢትዮጵያውያን መካከል ከባድ ብጥብጥ እንዲነሳ የመከፋፈሉን ተግባር ያካሄድ የነበረው የኤርትራው ግዛት ነው ። በኢትዮጵያ ውስጥ አስጨናቂና አስቸጋሪ የመንግሥት ግልበጣዎች እንዲጠነሰሱ አድርገናል ።….አብዛኛውም ቅስቀሳችን በትግሬዎችና በአማራዎች መሀል ጥላቻ እንዲፈጠር ነበር ። በተለይ በሸዋ…." በማለት ኢትዮፒያ ዲ ኦጂ በሚባለው መጽ ሐፉ ውስጥ ጽፎታል ።


በዝግጅቱ አለመሟላት አዝኖ የነበረው ደቦኖ በዝግጅቱ መሟላት ተደሰተ ። በኋላ ጊዜ በጻፈው መጽሐፉም ይህን ሁኔታ ያብራራና "….አሁን ሁሉም ተልኮል ናል ። በመጀመሪያ ዲቪዚዮናችን ውስጥ የነበሩት ወታደሮች በሚገባ የተመረጡ

... ሞቅ ባለች ጊዜ ወታደሩ ሁሉ እየዘመረ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ...።

... የጦሩን ሁኔታ የሚከታተሉና ታሪክ የሚጽፉ 300 ጋዜጠኞችና ... ነበሩ ። ጋዜጠኛው ቼስኮ ቶማሲሊ ስለዚያች ጊዜ ጉዞ በመጽሐፉ ሲገልጽ ...ህ ይላል ። "....መንገደኛው ወታደር ሁሉ እያንዳንዱ በሚያልፍበት ቦታ ...ር በጣቱ እያነሳ በምላሱ የአፈሩን ጣዕም ይቀምስ ነበር ። ይህም የአፈሩን ዓይ...ት ለማወቅና ለመለየት እያሉ ነው ። ይህን ምርምር የሚያደርጉበት ምክንያት ...ርነቱ በኋላ የሚያለሙትን መሬት ለመምረጥ ብለው ነው ። ከመጀመሪያው ...ምሮ ያገኙትንና የቀመሱትን ሁሉ ጥሩ አፈር ነው እያሉ ይነጋገራሉ ። እልፍ ...ሉ ቁጥር ደግሞ የተሻለ አፈር ያገኙና ይሄ የበለጠ ነው ይላሉ ። ይሄ ባመት ሁለቴ ...ል ይሰጣል ። ይሄ ደግሞ በዓመት ሶስቴ ሰብል ይሰጣል እያሉ እየተነጋገሩ ይጓ......" ብሏል ።

የኢጣሊያ ጦር ያለምንም ተከላካይ ተጓዘ ። የኢትዮጵያ መንግሥት የኢጣሊያ ...ንግሥት ወሰን አልፎ መጓዙን ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ አመለከተ ። ኢጣሊያ መረብን ...ንዳትሻገር እንዲከላከሉ ራስ ሥዩም ታዘው ነበር ። ራስ ሥዩም ግን በሥፍራው ...ልተገኙም ።


———O———



ወደኢትዮጵያ የሚጓዘው የኢጣሊያ ወታደር ስዊዝ ካናልን በመርከብ ሲያልፍ ።



ወደ ኢትዮጵያ የሚዘምተው የኢጣሊያ ወታደር ናፖሊ ውስጥ በሰልፍ ሲያልፍ






በመርከብ የመጣው የኢጣሊያ አይሮፕላን ምፅዋ ላይ ሲራገፍ ።




የኢጣሊያ ወታደር ሞቃዲሾ ደረሰ ።




ምፅዋ ላይ ስንቅ ተራገፈ ።




ምፅዋ ወደብ የወረደው የኢጣሊያ ጦር ።



የኢጣሊያ ወታደሮች ምፅዋ ላይ ከመርከብ ሲወርዱ ።




ለውጊያ የመጡ የኢጣሊያ ፈረሶች ምፅዋ ላይ ከመርከብ ሲራገፉ።



ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ ጦር ማንሳቱን ለኢጣሊያ ሕዝብ ሲገልፅ ።




በዘመኑ እጅግ ዘመናዊ የነበሩት የኢጣሊያ ታንኮች በኢትዮጵያ መሬት ላይ



ለአስቸጋሪ መንገድ የተሰለፉት መኪናዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሲጓዙ ።




የኢጣሊያ ወታደር የመረብን ወንዝ ሲያቋርጥ ።



መቃዲሾ ላይ የተከመረ ቦምብ ።



ባለሰንሰለት እግሮቹ ታንኮች ወደ መሀል ኢትዮጵያ ሲጓዙ ።




አይሮፕላናቸው በተፈለገው አቅጣጫ የሚዞር መትረየስ ነበረው ።




ከመጓጓዣ መኪናዎቻቸው ጥቂቶቹ ።




አይሮፕላኖች ቦምብ ሲጫኑ (አስመራ)።




አይሮፕላኖች የመርዝ ጋዝ ሲጫኑ (አሥመራ)።




ለምሽግ መስሪያ ባለእሾህ ሽቦ የተጫኑ መኪናዎች ።



የወታደሩን ሞራል የሚገነባው ክፍል በጦር ሜዳ መዝናኛ ሲያዘጋጅ ።




ምግብ ሰሪው ክፍል



ምፅዋ ላይ የተከማቸው ስንቅ ወደጦር ግንባር ሲጋዝ



ኤርትራ ውስጥ ወደ ወሰን የሚወስደው መንገድ ሲሠራ ።



ጊዜያዊው መሸጋገሪያ ድልድይ

# ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የአጼ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ነው ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ተሞላቶ ያደገ መስፍን በመሆኑ በልጅነቱም "....በጣም ጠጪ ነበረ ።...." ይለዋል ሞስሌ በመጽሐፉ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን እንደያዙ ትግራይን ለሁለት ከፍለው ለራስ ስዩምና ለኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በገዢነት ሰጧቸው ። በዚያም ላይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ገና ለጋብቻ ያልደረሰች ልጃቸውን ዘነበወርቅን (ብዙ ፀሐፊዎች 13 ዓመቷ ነበረ ይላሉ) ለኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በሚስትነት ዳሩለት "...ስካራም ባልዋ እያበሳጨና እየደበደበ ሊያኖራት አልቻለም...." ይላል ሞስሌ ። ልጅቱም በወሊድ ምክንያት ሞተች ።

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ "ግዛት እንሶኛልና ትግራይ በሙሉ ተጠቃሎ ይሰጠኝ" በማለት አመለከተ ። ንጉሱም "ሁሉን ለማስተዳደር አትችልምና ከስዩም ጋር እየተረዳዳችሁ ግዙ" አሉት ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በአማችነቱ ሁልጊዜ ወደ አዲስ አበባ ይመላለሳል ። ወደ አዲስ አበባ የሚመላለሰውም በአስመራ ዞሮ በመርከብ ወደጂቡቲ ሄዶ ፤ ከጂቡቲ በባቡር ተሳፍሮ አዲስ አበባ ይገባል ። ኤርትራ ወሰን በሚደርስበት ጊዜ የኢጣሊያ መኪና ተቀብሎ አስመራ ያገባዋል ። ሲመለስም ከባህር ጠረፍ እስከ ትግራይ ወሰን በኢጣሊያ መኪና ይጓዛል ።

ደቦና በመጽሐፉ "...ጉግሳ የንጉሡ ንጉሥ ቤት ልጅ ባል ነው ። ግን ያሞ እመፀኛ ነው ።.... በትግሬ በተሾሙት በራስ ስዩምና በሱ መሀል ቅራኔ አለ ።....የስላ ጓዶቻችንና እድሞ ያለውም ቆንሲላችን ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኛ ወገን እንዲሆን አድርገውታል ።....አስመራ መጥቶ የኛ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ሹመት እንድሰጠው ጠየቀኝ ። ....ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነቱን እስትንጀምር ድረስ እሺ እያልኩ አቆየሁት ። ....እንቁላል ለመጥበስ መጥበሻውን ከማዘጋጀታችን በፊት እንቁላሉን እንዳልሰበር ብዬ ነው ። ስለዚህ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን ግድየለም ታገስ ብቻ....ቀኑ በደረሰ ጊዜ ያልከውን ሁሉ አደርግልሃለሁ እያልኩ አቆየሁት ።..." ይላል ።

በአሥመራ የኢትዮጵያ ቆንሲል የነበሩት ወዳጆ ዓሊ ወደ አዲስ አበባ መ ተው ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኢጣሊያኖች ጋር መወዳጀቱንና ከኢጣሊያኖችም ደሞ እንደሚከፈለው በበቂ ማስረጃ አስረድተው ለንጉሡ አመለከቱ ። ንጉሡ ነገሥቱም "...አሁን ያለው የኢትዮጵያ መኳንንት አብዛኛው ከኢጣሊያ ገንዘብ ይቀበላል ። ይህም የኢጣሊያን ኢኮኖሚ ለመጉዳት እንጂ እኛን ለመክዳት አይደለም ። ሁሉም ከኛው ጋር ናቸውና የኃይለ ሥላሴ ጉግሳም እንደዚሁ ነው ..." ብለው የወዳ ዓሊን ሪፖርት ሳይቀበሉ ቀሩ ።

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ጦርነቱ ሊነሳ አቅራቢያ መስከረም 28 ቀን ከአዲስ አበባ ጋር የሚያገናኘውን የስልክ መስመር በሙሉ በጣጥሶ በወታደሮቹ ታጅቦ የአሥመራ ጉዞውን ጀመረ ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ወደ ኢጣሊያኖች ከመግባቱ በፊት 12000 ወታ ደሮች ነበሩት ። ኢትዮጵያን ከድቶ ወደ ኢጣሊያ ሲገባ ግን እሱንም ሠራዊቱ ከድ ቶት ታጅቦ የገባው በአንድ ሺ ወታደር ያህል ነው ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ እዳ ሐሙስ ላለው የኢጣሊያ ጦር እጁን ቢሰጥ ለኢጣሊያ መንግሥት ከልብ ለማገልገል መምጣቱን ነገረ ።

# የኢትዮጵያ ጦር

የኢትዮጵያን ወታደር ብዛት ዊልያም ማኪን ሲገልጽ ከነጀሌው 700 000 ያደርሰውና "...ከኪ. ለብሶ የሚታየው የሰለጠነው ወታደር ግን 25,000 ይሆናል" ይላል ። ይህ እንግዲህ በጠቅላላ ለኢጣሊያ የተሰለፈው ጦር ነው ። ኢጣሊያኖች በሰጡት ግምት የኢትዮጵያ ወታደር 350 000 ነው ይሉና 400 000 ጠመንጃ በያይነቱ ፤ 200 መድፍ ፤ አምሳ ቀላልና ከባድ አርሊኮን (ፀረ አይሮፕላን) አላቸው ብለዋል ። ሊዎናርድ ሞስሌ እንደፃፈው ደግሞ የኢትዮጵያ ጦር 200 ትናንሽ የተለያዩ መድፎች ፤ ለእያንዳንዱ መድፍም 500 ጥይት ፤ 3500 መትረየስ ፤ 15 አይሮፕላን ፤ ለስምንት ወር ከሚበቃ ቤንዚን ጋር ኢትዮጵያውያን ነበራቸው ብሏል ።

ወደፊት በየጦሩ ቦታ ለመግለጽ እንደምሞክረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ለመሆን የበቃው በጦር መሪዎቹ የአመራር ችሎታ ማነስና ጠላትን በመናቃቸው ነው ። እያንዳንዱ መኳንንትም የርስ በርስ ቁርሾ ስላለበት አንዱ አንዱን በማጋፈጥ ፤ በጦር ሜዳ ላይ ሹም ሽር በማድረግ ፤ ለዘውዱና ለሥልጣን የነበራቸው ሽሚያ ሁሉ ተጨምሮ ሕዝቡን ባንድነት ሊያስተባብረው ባለመቻሉ ኢጣሊያ ድል ለማድረግ ቻለች ። ይህን የኢጣሊያ ጦር መሪዎች ሁሉ አምነውበታል ።

የዚያን ጊዜውን የሁሉንም አሳብ አሁን መናገር አይቻልም እንጂ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ጦር መሪ ምን ዓይነት ስህተት እንዳደረገ አለፍ አለፍ እያልን በመጠኑ እናየዋለን ። የኢትዮጵያ ጦር አማካሪ የነበረው ሩሲያዊው ኮሎኔል ኮኖቫሎፍ (T.E. Konovaloff) በመጽሐፉ "... ራስ ሥዩም የተከበሩና ክብራቸውን የሚጠብቁ ሰው ናቸው ...የቶፖግራፊ ካርታ ሳሳያቸው በዚህ ጉዳይ አትጨነቅ ። አልፈልግውም ። የካርታ ጉዳይ ስሜት ያለው ራስ ካሣ ነው ። በእነሱም ላይ ካርታ ብቻ ሲመለከት ብዙ ሰዓት ያጠፋል ። ለኔ ግን ምንም ስሜት አይሰጡኝም ። በዚህ ምክንያትም እባክህ አታስቸግረኝ ይሉኛል ..." ሲል ጽፏል ። ኮኖቫሎፍ የሚያቀርበው ካርታ የኢጣሊያ ጦር በየት ቢመጣ በየት በኩል መግጠም እንደሚቻል የሚያስረዳ ነበር ። ግን ተቀባይ አጥቶ ጦሩ እንደ ዝንጀር ገደል እየዘለለ እንዲዋጋና እንዲያልቅ ሆነ ።

በዶቦና ቦታ የተተካው ዋናው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ማረሻል ባዶሊዮም ቢሆን በኋላ ጊዜ ባሳተመው መጽሐፉ የኢትዮጵያውያንን ጦር መሪዎች ሁኔታ ገልጾታል ። "...የኢትዮጵያ ጦር አዛገሮች በሙሉ የጦር አዛዥነት ችሎታ ፈጽሞ የላቸውም... ጉዳዩን ሁሉ በቀላሉ የሚገምቱና የሚመገዱቁ ናቸው..." ብሏል ።

የባዶሊዮ የቅርብ ረዳት የነበረው ጄኔራል ኳሪኖ አርሜሊኒ (Quivrino Armellini) ስለኢትዮጵያውያን ጦር መሪዎች ሲገልጽ "....ራስ ካሣ ፤ ራስ ሙሉጌታ ፤ ራስ ስዩምና ራስ እምሩ ስለ ጦርነት የተማሩት ትምህርት የለም ።... ታላቅ ሰውነታቸው ብቻ ለጦር አዝማችነት አበቃቸው ። ...ምንም አይነት የጦር ትምህርት ሳይኖራቸው ፤ በዘመናዊ የጦር ትምህርት የሰለጠነውን ወታደር ፤ ዘመናዊውን መሣሪያና ዘመናዊ ጦር አዛገሮችን እንዲገጥሙ ታዘዙ ። ይህ ነው ድል ለመሆን ያበቃቸው ምክንያት..." ብሏል ።

ባዶሊዮ ስለራስ ካሣ ሲጽፍ "... የማዘዝ ልምድ የለውም ። በደህና ጦርነት ቦታ ውሎ ደህና ውጊያ እንኳ አላየም ። ሌላው ቀርቶ የራሱን ወታደሮች እንኳን ሥራ ማሠራት አይችልም ። ወታደሮቹ ግን ምርጥ ምርጦች ናቸው ። ባለፈውም ሆነ አሁን የአበሻ ጦር መሪዎች ከፊታቸው ካለው ጠላት ይልቅ ከኋላ የቀረውን ወዳ

ጃቸውን ይፈራሉ ። በዚህም ፍራቻ ምክንያት ያላቸውን ኃይል ሁሉ ባንድነት ሰብስበው ከጠላት ጋር አይታገሉበትም ። ከኃይላቸው ግማሹ ተከፍሎ በመንደር ይቀርና የጌታውን ክብር እንዲጠብቅ ይደረጋል ...” ብሏል ። በሌላው የመጽሐፉ ገጽ ላይ ደግሞ ባዶሊዮ ይህንኑ ጉዳይ አንስቶ “...በኢትዮጵያውያን ጦር መሪዎች መሀል መለያየትና የውስጥ መጠራጠር እንደተፈጠረው ሁሉ ወታደሩም ጌታውን እየተከተለ ተሸካክሯል ። ለዚህ ሁሉ መለያየት ያበቁት ንጉሡ ናቸው ።... ራስ ስዩም ፣ የግል ጉዳይ የሆነ የማዕረግ ነገር ቂም አለባቸው ። ራስ ካሣ ጥሩ የቤተ ክርስቲያን ሰው ናቸው ። ሙሉጌታ ጦረኛና በጦር ያደገ ሰው ነው ። በዚህም በጦረኛነቱ ምክንያት ጠቅላይ የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ ሆኖ ተሾሞ ነበር ...” ብሏል ።

ባዶሊዮ ራስ ሙሉጌታን “... ተሾሞ ነበር...” ያለው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ የነበሩት ራስ ሙሉጌታ ተሽረው ራስ ካሣ ከተሾሙ በኋላ ያተተው ነው ። ስለራስ ሙሉጌታ መሻርና ስለራስ ካሣ መሾም ባርከር ሲጽፍ “...ንጉሡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከታላላቅ ሰዎች የተወለዱ ናቸው እንጂ የጦር አመራር ችሎታ ያላቸው አይደሉም ። ለመጀመሪያ ጊዜ ጦርነቱ ውስጥ ለመግባት ደሴ ሲደርሱ የሥራ መጀመሪያ ያደረጉት ራስ ሙሉጌታን ሽረው የቅርብ ወዳጃቸውን ራስ ካሣን መሾም ነበር ። የጦር ሚኒስትሩ (ራስ ሙሉጌታ) የታወቀ ጉበዝ ሰው ነበር ። የሚጠበቀውና የሚፈራውም የሱ ጦር አመራር ነበር ። የወታደሮች ወታደር ነበር ። ራስ ካሣ ግን ምንም የጦር ጥበብ የማያውቅ ሰው ነው ። ከነገሥታት ትውልድና በፖለቲካም ተሰሚነት ስላለው ብቻ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ሆነ ። ለዚህ ነው ባዶሊዮ የሙሉጌታን መሻርና የካሣን መሾም ሲሰማ የተደሰተው ።...” ካለ በኋላ በሌላ የመጽሐፉ ገጽ ደግሞ “... ሙሉጌታ ተሽሮ ካሣ ሲሾም አምባራዶም ያለው ሙሉጌታና ጐንደር ያለው እምሩ የካሣን ትእዛዝ ላለመስማት ጆሮአቸውን ደፈኑ ። ሙሉጌታ የሚደርሰውን ትእዛዝ እንዳልሰማ እየሆነ ምንም የሰማሁት የለም ይላል ። እምሩም የተነሳብኝን ያዤ ውስጥ ሽፍታ በመከላከል ላይ ነኝ እያለ አይታዘዝም ። የካሣ ትእዛዝ ተቀባይ አጣ ። እንዚህ ሁለት ታላላቅ ጦረኞች የሚያስቡት አሳብ ካሣ የሚገጥመውን ግጥም እንዲዋረድና ክፍ ያደረገው የንጉሡ ዓይን ዝቅ እንዲያደርገው ነው...” በማለት ይተነትናል ።

ባርከር “...የተፈራው ጦር የሙሉጌታ ነበር...” ያለው እውነቱን ነው ። ይህን ነገር የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ባዶሊዮም በመጽሐፉ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል “...የጦር ሚኒስትሩ ሽማግሌው ራስ ሙሉጌታ በአድዋ ዘመቻ ክንዱን ያሳየ በመሆኑ የኢትዮጵያን ጦር ፈርተን ብዙ መሣሪያ አከማችተን ነበር ። ጦርነቱ እንደተጀመረ ንጉሡ ፣ ራስ ሙሉጌታን ሽረው ቂሱን ራስ ካሣን የጦር ሚኒስትር አድርገው በመሾማቸው የኢጣሊያ ጦር በቀላሉ ድል እንደሚያደርግ ገብቶን ተደሰትን ። በመኳንንቱ መሐል ባለው የርስ በርስ ያለ መግባባትም ተጠቀምን ። ንጉሡም የራስ ሙሉጌታን ሠራዊት እንዲከዳ ስላደረጉ ራስ ሙሉጌታን ከጥቂት ከተረፉት ታማኝ ወታደሮቹ ጋር አሻል በረሃ ውስጥ አግኝተን በአይሮፕላን መትረየስ ገደልነው ። በዚህም በሙሉጌታ ሞት የኢትዮጵያውያንን ሞራል ሰበርነው...”

በኢትዮጵያውያን መሀል ባለው ያለመግባባትና መለያየት ምክንያት ከውጭ አገር ኢትዮጵያን ለመርዳት የተነሱና በኢጣሊያ ግፈኛነት የተበሳጩ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ተቀባይ አጡ ። ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ባወጀች ጊዜ ከእንግሊዝ አገር ብቻ ሶስት ሺ ሰዎች ኢትዮጵያን ለመርዳት በወዶ ዘማችነት ተመዝግበው ነበር ። እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 4 ቀን 1935 ዓም የወጣው ዴይሊ ኤክስፕሬስ ጋዜጣ “...ንጉሡ ይህን እርዳታ አልተቀበሉትም ። ያልተቀበሉበትም ዋናው ምክንያት ለእነዚህ ሰዎች የሚከፈል ነገር የለም ብለው ነው ። ከኢትዮጵያውያን ጐን ተሰልፈን እንዋጋለን ያሉት እንግሊዞች ብቻ ሳይሆኑ በራንግል አርሚ ውስጥ የነበሩና ከነራቸው የከዱ ሩሲያውያን ፣ ቱርኮች ፣ ሁንጋሪያውያኖችና ቼኮዝሎቫኪያን

ሁሉ ናቸው ።...” ብሏል ። ይህ ብቻ ሳይሆን በኒውዮርክ ከተማ ያሉ አሜሪካውያን በሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት የኢጣሊያን አድራጎት ተቃወሙ ። በማዲሰን አደባባይ የተሰበሰቡ ዘጠኝ ሺ አሜሪካውያን የሙሶሊኒን ፎቶግራፍ በማቃጠል ተቃውሞአ ቸውን ገለጡ ። በኢጣሊያ ውስጥም ቢሆን ሳይፈሩ አድራጎቱን የተቃወሙ ሰዎች ነበሩ ። በጀርመን ሲኒማ ቤቶችም የሙሶሊኒን ጦር ማጋዝና ማከማቸት የሚያሳየው “ኢትዮፒያ 1935” የተባለው ፊልም ለሕዝብ እየታየ ሕዝቡ ተቃውሞውን ይገ ልጽ ነበር ። በካይሮም የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች በየመስጊዱ ሕዝቡን እየ ሰበሰቡ ኢትዮጵያን በግፍ ከመጣባት መከራ እንዲያድናት እንዲፀልይ አዘዙ ።

ይህ ሁሉ ቢሆንም ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሪዎች ስህተትና በመሣሪያ እጥረት ድል እየሆነ ይሄድ ጀመር ። ባዶሊዮ ራሱ ሲመሰክር “... የኢጣሊያ አይሮ ፕላኖች ዘመናዊና ባለሙሉ ትጥቅ ባይሆኑ ኖሮ ኢትዮጵያውያን የአድዋውን ድል እንደገና ይደግሙ ነበር ። በፓይለቶቻችን ታላቅ ተግባር ኢጣሊያኖች ድል ለማድ ረግ በቃን ።...” ብሏል ። ይህንንም ወደፊት በየጦሩ ግንባር እናገኘዋለን ።

———O———




የክብር ዘበኛ ጦር

...ቆቃ ሞቅ ባለች ጊዜ ወታደሩ ሁሉ እየዘመረ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ...።

... የጦሩን ሁኔታ የሚከታተሉና ታሪክ የሚጽፉ 300 ጋዜጠኞችና ... ነበሩ ። ጋዜጠኛው ቼስኮ ቶማሲሊ ስለዚያች ጊዜ ጉዞ በመጽሐፉ ሲገልጽ ... ይላል ። "....መንገደኛው ወታደር ሁሉ እያንዳንዱ በሚያልፍበት ቦታ ... በጣቱ እያነሳ በምላሱ የአፈሩን ጣዕም ይቀምስ ነበር ። ይህም የአፈሩን ዓይ... ለማወቅና ለመለየት እያሉ ነው ። ይህን ምርምር የሚያደርጉበት ምክንያት ...ርነቱ በኋላ የሚያለሙትን መሬት ለመምረጥ ብለው ነው ። ከመጀመሪያው ...ሮ ያገኙትንና የቀመሱትን ሁሉ ጥሩ አፈር ነው እያሉ ይነጋገራሉ ። እልፍ ... ቁጥር ደግሞ የተሻለ አፈር ያገኙና ይሄ የበለጠ ነው ይላሉ ። ይሄ ባመት ሁለቴ ...ል ይሰጣል ። ይሄ ደግሞ በዓመት ሶስቴ ሰብል ይሰጣል እያሉ እየተነጋገሩ ይጓ...…" ብሏል ።

የኢጣሊያ ጦር ያለምንም ተከላካይ ተጓዘ ። የኢትዮጵያ መንግሥት የኢጣሊያ ...ንግሥት ወሰን አልፎ መጓዙን ለሊግ ኦፍ ኔሽንስ አመለከተ ። ኢጣሊያ መረብን ...ንዳትሻገር እንዲከላከሉ ራስ ሥዩም ታዘው ነበር ። ራስ ሥዩም ግን በሥፍራው ...ልተገኙም ።


———o———



ወደኢትዮጵያ የሚጓዘው የኢጣሊያ ወታደር ስዊዝ ካናልን በመርከብ ሲያልፍ ።



ወደ ኢትዮጵያ የሚዘምተው የኢጣሊያ ወታደር ናፖሊ ውስጥ በሰልፍ ሲያልፍ







በመርከብ የመጣው የኢጣሊያ አይሮፕላን ምፅዋ ላይ ሲራገፍ ።




የኢጣሊያ ወታደር ሞቃዲሾ ደረሰ።




ምፅዋ ላይ ስንቅ ተራገፈ።




ምፅዋ ወደብ የወረደው የኢጣሊያ ጦር ።



የኢጣሊያ ወታደሮች ምፅዋ ላይ ከመርከብ ሲወርዱ ።




ለውጊያ የመጡ የኢጣሊያ ፈረሶች ምፅዋ ላይ ከመርከብ ሲራገፉ ።



ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ ጦር ማንሳቱን ለኢጣሊያ ሕዝብ ሲገልፅ ።




በዘመኑ እጅግ ዘመናዊ የነበሩት የኢጣሊያ ታንኮች በኢትዮጵያ መሬት ላይ



ለአስቸጋሪ መንገድ የተሰለፉት መኪናዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሲጓዙ ።




የኢጣሊያ ወታደር የመረብን ወንዝ ሲያቋርጥ ።



መቃዲሾ ላይ የተከመረ ቦምብ ።



ባለሰንሰለት እግሮቹ ታንኮች ወደ መሀል ኢትዮጵያ ሲጓዙ ።



አይሮፕላናቸው በተፈለገው አቅጣጫ የሚዞር መትረየስ ነበረው ።





ከመጓጓዣ መኪናዎቻቸው ጥቂቶቹ ።



አይሮፕላኖች ቦምብ ሲጫኑ (አስመራ) ።




አይሮፕላኖች የመርዝ ጋዝ ሲጫኑ (አሥመራ) ።




ለምሽግ መስሪያ ባለእሾህ ሽቦ የተጫኑ መኪናዎች ።



የወታደሩን ሞራል የሚገነባው ክፍል በጦር ሜዳ መዝናኛ ሲያዘጋጅ ።




ምግብ ሰሪው ክፍል




ምፅዋ ላይ የተከማቸው ስንቅ ወደጦር ግንባር ሲጋዝ



ኤርትራ ውስጥ ወደ ወሰን የሚወስደው መንገድ ሲሠራ።



ጊዜያዊው መሸጋገሪያ ድልድይ



ለድል መልካም ዕድል አለው የተባለው ጥቁር አሣማ በታንክ ተጭኖ ይጓዝ ነበር ።

# ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የአጼ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ነው ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ተምላቆ ያደገ መስፍን በመሆኑ በልጅነቱም "....በጣም ጠጪ ነበረ ።...." ይለዋል ሞስሌ በመጽሐፉ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን እንደያዙ ትግራይን ለሁለት ከፍለው ለራስ ስዩምና ለኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በገዢነት ሰጧቸው ። በዚያም ላይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ገና ለጋብቻ ያልደረሰች ልጃቸውን ዘነበወርቅን (ብዙ ፀሐፊዎች 13 ዓመቷ ነበረ ይላሉ) ለኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በሚስትነት ዳሩለት "...በካራም ባልዋ እያበሳጨና እየደበደበ ሊያኖራት አልቻለም...." ይላል ሞስሌ ። ልጅቱም በወሊድ ምክንያት ሞተች ።

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ "ግዛት እንሶኛልና ትግራይ በሙሉ ተጠቃሎ ይሰጠኝ" በማለት አመለከተ ። ንጉሱም "ሁሉን ለማስተዳደር አትችልምና ከስዩም ጋር እየተረዳዳችሁ ግዙ" አሉት ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ በአማችነቱ ሁልጊዜ ወደ አዲስ አበባ ይመላለሳል ። ወደ አዲስ አበባ የሚመላለሰውም በአስመራ ዞሮ በመርከብ ወደጂቡቲ ሄዶ ፤ ከጂቡቲ በባቡር ተሳፍሮ አዲስ አበባ ይገባል ። ኤርትራ ወሰን በሚደርስበት ጊዜ የኢጣሊያ መኪና ተቀብሎ አስመራ ያገባዋል ። ሲመለስም ከባህር ጠረፍ እስከ ትግራይ ወሰን በኢጣሊያ መኪና ይገባል ።

ደቦኖ በመጽሐፉ "....ጉግሳ የንጉሠ ነገሥቱ ሴት ልጅ ባል ነው ። ግን ያሞ እመፀኛ ነው ።.... በትግሬ በተሾሙት በራስ ስዩምና በሱ መሀል ቅራኔ አለ ።....የስለላ ጓዶቻችንና አድዋ ያለውም ቆንሲላችን ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኛ ወገን እንዲሆን አድርገውታል ።....አስመራ መጥቶ የኛ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ሹመት እንድሰጠው ጠየቀኝ ።....ከኢትዮጵያ ጋር ግጭቱን እስትንጀምር ድረስ እሺ እያልኩ አቆየሁት ።....እንቁላል ለመጥበስ መጥበሻውን ከማዘጋጀታችን በፊት እንቁላሉን እንዳልሰብር ብዬ ነው ። ስለዚህ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን ግድየለም ታገስ ብቻ....ቀኑ በደረሰ ጊዜ ያልከውን ሁሉ አደርግልሃለሁ እያልኩ አቆየሁት ።..." ይላል ።

በአሥመራ የኢትዮጵያ ቆንሲል የነበሩት ወዳጆ ዓሊ ወደ አዲስ አበባ መተው ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኢጣሊያኖች ጋር መወዳጀቱንና ከኢጣሊያኖችም ደሞ እንደሚከፈለው በበቂ ማስረጃ አስረድተው ለንጉሡ አመለከቱ ። ንጉሡ ነገሥቱም "...አሁን ያለው የኢትዮጵያ መኳንንት አብዛኛው ከኢጣሊያ ገንዘብ ይቀበላል ። ይህም የኢጣሊያን ኢኮኖሚ ለመጉዳት እንጂ እኛን ለመክዳት አይደለም ። ሁሉም ከኛው ጋር ናቸውና የኃይለ ሥላሴ ጉግሳም እንደዚሁ ነው ..." ብለው የወዳጆ ዓሊን ሪፖርት ሳይቀበሉ ቀሩ ።

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ጦርነቱ ሊነሳ አቅራቢያ መስከረም 28 ቀን ከአዲስ አበባ ጋር የሚያገናኘውን የስልክ መስመር በሙሉ በጣጥሶ በወታደሮቹ ታጅቦ የአሥመራ ጉዞውን ጀመረ ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ወደ ኢጣሊያኖች ከመግባቱ በፊት 12000 ወታደሮች ነበሩት ። ኢትዮጵያን ከድቶ ወደ ኢጣሊያ ሲገባ ግን አሉንም ሠራዊቱ ከድቶት ታጅቦ የገባው በአንድ ሺ ወታደር ያህል ነው ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ አዳጋ ሐሙስ ላለው የኢጣሊያ ጦር እጁን ሲሰጥ ለኢጣሊያ መንግሥት ከልብ ለማገልገል መምጣቱን ነገረ ።

ደቦኖ በመጽሐፉ ስለ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ አመጣጥ ሲገልጥ "...ኦክቶበር 8 ቀን ጀኔራል ሳንቲኒ በላከብኝ መልእክት ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኛ እርዳታ መፈለጉንና መቀሌ ውስጥ 7000 ሰዎች ይዞ የተቀመጠውን ደጃዝማች ኃይሉ ከበደን ለመውጋት መጠየቁን ላከብኝ ። ...ኦክቶበር 10 ቀን ጧት ጀኔራል ሳንቲኒ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎቹን ይዞ በኛ መስመር ለማለፍ ጠይቋልና ምን ላድርግ? ብሎ ላከብኝ። እኔም መምጣቱን ይምጣ ፤ ግን አንድ ዓይንህን ጣልበት አልኩት ።...ቀትር ሲሆን የአየር ክፍላችን እንዳስረዳኝ ባረጅም ሰልፍ በሰላም እንደሚጓዝና በጓዙም ውስጥ ከብቶች መኖራቸውንና ጉዞውም ከመቀሌ ተነስቶ በአዲግራት በኩል ለማለፍ ከመሀል መድረሱን ነገሩኝ ። በአራት (በኛ 10) ሰዓት ከአንደኛ ክፍለ ጦር በራዲዮ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ 1200 ሰዎች ፤ 8 ጥሩ መትረየሶች ይዞ አዲግራት መግባቱን ነገሩኝ ። ይህንንም ወደ ሮም ሳስታውቅ 10 000 ወታደሮች አሉት የተባለው እያባ ሉት ነው ብዬ መምጣቱን ነገርኩ ። ለጀኔራል ሳንቲኒም በሚቀጥለው ቀን ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከኔ ዘንድ መጥቶ እንድንገናኝ እንዲያደርግ በቴሌግራም አሳወቅሁት ።

"ኦክቶበሬ 12 ቀን በ11 (በኛ 5) ሰዓት ኮአቲት ደረሰ ። እኔም በጉጆዬ ውስጥ ተቀበልኩት ። እሱም መከፋቱን ነገረኝ ። ስለ ጉዳዩም አንዳንድ ፍንጭ አጫወተኝ ። በአበሻ ውስጥ ጦርነት የሚፈልግ ሰው እንደሌለና ጦርነቱን የሚፈልግ ንጉሡ ብቻ መሆኑን ነገረኝ... አሁን ፈጥናችሁ መቀሌን ብትይዙ በሰላም ገብታችሁ ትቀመጣላችሁ አለኝ ። እኔም ይሄን ለመወሰን የምችለው አቀርዳትን ጐብኝቼ ስመለስ ነው አልኩት ። ከዚያ በኋላ ስለኛ ወታደሮች ያለውን አስተያየት ጠየቅሁት ።

"እጅግ በጣም ታላቅ ዝግጅት ነው አለኝ ። በተለይ የሠራነው መንገድ እንዳስደሰተው ነገረኝ ። ...ሰዎችህ አሁን ባንተ ላይ ሙሉ እምነት አላቸውን? አልኩት ። እሱም በአምንታ ራሱን ነቅንቆ እንደነገርኳችሁ በጣም ጥሩ ነገር የሚሆነው በተቻለ ፍጥነት መቀሌ ብትገቡ ነው አለኝ ።..." ይለዋል ።

የዚህ ሰው መክዳት የኢትዮጵያን ጦር በብዙ መንገድ ጐድቷል ። አዲስ አበባ በሚመጣበት ጊዜና መቀሌም ሆኖ ንጉሠ ነገሥቱ የጦሩን ምስጢር ያጫውቱትና ያማክሩት ስለነበረ የኢትዮጵያን ጦር ሁኔታ በዝርዝር ያውቀዋል ። ይህንንም የሚያውቀውን የኢትዮጵያን ጦር ሁኔታ በዝርዝር ለዶቦኖ ነግሯል ። ኢንጂኘር ፈርናርድ ቤትሪ የተባለ የስዊስ ሰው ከደሴ አዲስ አበባ ድረስ የሚሠራው መንገድ ፕላን ነበረውና አብሮ ከድቶ ፕላኑንና መሰናክሎቹን ሁሉ የሚገልፀውን መመሪያ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ለዶቦኖ ሰጠ ። መቀሌ ድረስም ያለ ምንም ችግር በሱ መሪነት ኢጣሊያኖች መጓዝ እንደሚችሉ አስረዳ ። ራስ ስዩምም ምንም መከታና ረዳት ስለሌላቸው ከዋና ከተማቸው ከአድዋ በቀላሉ መግባት እንደሚቻል ለዶቦኖ አጫወተው ።

ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ባልከዱት ጥቂት ወታደሮቹ ታጅቦ ፤ ካኪ ልብሱን ለብሶ ፤ በሠራዊቱም መሀል ሃያ መትረየስ ፤ አራት የተራራ መድፍና ሁለት መለስተኛ ፀረ አይሮፕላን መትረየስ ይዞ ከደቦኖ ጋር ሲገናኝ ጀኔራል ደቦኖ ምስጢሩን ሁሉ ከሰማ በኋላ በኢጣሊያ ንጉስ በቪክቶር አማኑኤል ስም የትግራይ ጠቅላይ ገዥ ብሎ ሾመው።

ስለ ሹመቱ ጉዳይ ደቦኖ ሲገልጽ "...ሙሶሊኒ በቴሌግራም ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን የትግሬ ጠቅላይ ገዥ ብዬ እንድሾመው አሳወቀኝ ። አሳቡ ጥሩ አሳብ ነው ። ነገር ግን እኔ እንዳጣራሁት ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሕዝብ የሚያቅፈው ትልቅ ሰው አይደለም ። ተዋጊም አይደለም ።.... እንደ አባቱ እንኳ የማስተዳደር ችሎታ የለውም ። ቢሆንም ብዙ ወታደሮች በተሰበሰቡበት በንጉሣችን ስም ሹመቱን አወጅሁለት...." ብሏል ።

ከእኚህ ሰው ጋር በ1967 ዓም ተገናኝተን ስንጫወት "....በሰላም በግብርና እያረስሁ ለመኖር እንጂ ኢትዮጵያን ለመጉዳት አልከዳሁም..." ብለውኛል ። ውሸታቸውን ነው እንጂ በአምስቱ የፋሺስት ዘመናት የሠሩዋቸውና በየጊዜው የሚ

ሸለሟቸውን መዳሊያዎች የሚያወሱ የኢጣሊያ ጊዜ ጋዜጦች ከኔ ዘንድ በብዛት አሉ ።

ሙሶሊኒ ለዶቦኖ በሰጠው መልስ "...ደም መፍሰስ የሌለበት በፕሮፓጋንዳ ብቻ ድል አድርገው..." ስላለ በዶቦኖ ትእዛዝ ፤ በኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰባኪነት አንዳንድ የትግራይ ሹማምንት ለኢጣሊያ ገቡ ። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳም ካኪውን ለብሶ ፤ በቀይ ሐር ጥብጣብ በግራና በቀኝ ቁልቁል የተሰመረበትን ጠባብ ሱሪውን ታጥቆ ፤ ረጅም ቧት ጫማ አድርጎ ፤ የኢጣሊያኖችን ጠርቡሽ(ባርኔጣ) ራሱ ላይ ደፍቶ በአስመራ ከተማ ውስጥ እየተዘዋወረ ለሕዝብ ይታይ ጀመር ። ኢጣሊያውያኖችም በየቀኑ ሽቶና ሻምፓኝ ይሰጡት ጀመር ።

ጦርነቱ በተነሳ ጊዜ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ለኢጣሊያኖች እጅግ ጠቃሚ ሥራ የሠራና ቀንደኛ ተዋጊ ነበር ። በተለይም በመንገድ መምራት በኩል ብዙ አገልግሏል ። ይህንንም በመጠኑም ቢሆን ባለፈው ትርካዬ ውስጥ አልፎ አልፎ ገልጫለሁ ። ፣ አልፎ አልፎ ወደፊትም እገልጻለሁ ።

# የኢትዮጵያ ጦር

የኢትዮጵያን ወታደር ብዛት ዊልያም ማኪን ሲገልጽ ከነጀሌው 700 000 ያደርሰውና "...ከኪ. ለብሶ የሚታየው የሰለጠነው ወታደር ግን 25,000 ይሆናል" ይላል ። ይህ እንግዲህ በጠቅላላ ለኢጣሊያ የተሰለፈው ጦር ነው ። ኢጣሊያኖች በሰጡት ግምት የኢትዮጵያ ወታደር 350 000 ነው ይሉና 400 000 ጠመንጃ በያይነቱ ፤ 200 መድፍ ፤ አምሳ ቀላልና ከባድ አርሊኮን (ፀረ አይሮፕላን) አላቸው ብለዋል ። ሊዎናርድ ሞስሌ እንደጻፈው ደግሞ የኢትዮጵያ ጦር 200 ትናንሽ የተለያዩ መድፎች ፤ ለእያንዳንዱ መድፍም 500 ጥይት ፤ 3500 መትረየስ ፤ 15 አይሮፕላን ፤ ለስምንት ወር ከሚበቃ ቤንዚን ጋር ኢትዮጵያውያን ነበራቸው ብሏል ።

ወደፊት በየጦሩ ቦታ ለመግለጽ እንደሞከርነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ለመሆን የበቃው በጦር መሪዎቹ የአመራር ችሎታ ማነስና ጠላትን በመናቃቸው ነው ። እያንዳንዱ መኳንንትም የርስ በርስ ቁርሾ ስላለበት አንዱ አንዱን በማጋፈጥ ፤ በጦር ሜዳ ላይ ሹም ሽር በማድረግ ፤ ለዘውዱና ለሥልጣን የነበራቸው ሽሚያ ሁሉ ተጨምሮ ሕዝቡን ባንድነት ሊያስተባብረው ባለመቻሉ ኢጣሊያ ድል ለማድረግ ቻለች ። ይህን የኢጣሊያ ጦር መሪዎች ሁሉ አምነውበታል ።

የዚያን ጊዜውን የሁሉንም አሳብ አሁን መናገር አይቻልም እንጂ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ጦር መሪ ምን ዓይነት ስህተት እንዳደረገ አለፍ አለፍ እያልን በመጠኑ እናየዋለን ። የኢትዮጵያ ጦር አማካሪ የነበረው ሩሲያዊው ኮሎኔል ኮኖቫሎፍ (T.E. Konovaloff) በመጽሐፉ "... ራስ ሥዩም የተከበሩና ክብራቸውን የሚጠብቁ ሰው ናቸው ...የቶፖግራፊ ካርታ ሳሳያቸው በዚህ ጉዳይ አትጨነቅ ። አልፈልገውም ። የካርታ ጉዳይ ስሜት ያለው ራስ ካሣ ነው ። በእነሱም ላይ ካርታ ብቻ ሲመለከት ብዙ ሰዓት ያጠፋል ። ለኔ ግን ምንም ስሜት አይሰጡኝም ። በዚህ ምክንያትም እባክህ አታስቸግረኝ ይሉኛል ..." ሲል ጽፏል ። ኮኖቫሎፍ የሚያቀርበው ካርታ የኢጣሊያ ጦር በየት ቢመጣ በየት በኩል መግጠም እንደሚቻል የሚያስረዳ ነበር ። ግን ተቀባይ አጥቶ ጦሩ እንደ ዝንጀሮ ገደል እየቧጠጠ እንዲዋጋና እንዲያልቅ ሆነ ።

በዶቦና ቦታ የተተካው ዋናው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ማረሻል ባዶሊዮም ቢሆን በኋላ ጊዜ ባሳተመው መጽሐፉ የኢትዮጵያውያንን ጦር መሪዎች ሁኔታ ገልጾታል ። "...የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች በሙሉ የጦር አዛዥነት ችሎታ ፈጽሞ የላቸውም... ጉዳዩን ሁሉ በቀላሉ የሚገምቱና የሚመፃደቁ ናቸው..." ብሏል ።

የባዶሊዮ የቅርብ ረዳት የነበረው ጄኔራል ኳሪኖ አርሜሊኒ (Quivrino Armellini) ስለኢትዮጵያውያን ጦር መሪዎች ሲገልጽ "....ራስ ካሣ ፤ ራስ ሙሉጌታ ፤ ራስ ስዩምና ራስ እምሩ ስለ ጦርነት የተማሩት ትምህርት የለም ።... ታላቅ ሰውነታቸው ብቻ ለጦር አዝማችነት አበቃቸው ። ...ምንም አይነት የጦር ትምህርት ሳይኖራቸው ፤ በዘመናዊ የጦር ትምህርት የሰለጠነውን ወታደር ፤ ዘመናዊውን መሣሪያና ዘመናዊ ጦር አዛዦችን እንዲገጥሙ ታዘዙ ። ይህ ነው ድል ለመሆን ያበቃቸው ምክንያት..." ብሏል ።

ባዶሊዮ ስለራስ ካሣ ሲጽፍ "... የማዘዝ ልምድ የለውም ። በደህና ጦርነት ቦታ ውሎ ደህና ውጊያ እንኳ አላየም ። ሌላው ቀርቶ የራሱን ወታደሮች እንኳን ሥራ ማሠራት አይችልም ። ወታደሮቹ ግን ምርጥ ምርጦች ናቸው ። ባለፈውም ሆነ አሁን የአበሻ ጦር መሪዎች ከፊታቸው ካለው ጠላት ይልቅ ከኋላ የቀረውን ወዳ

ጃቸውን ይፈራሉ ። በዚህም ፍራቻ ምክንያት ያላቸውን ኃይል ሁሉ ባንድነት ሰብስበው ከጠላት ጋር አይታገሉበትም ። ከኃይላቸው ግማሹ ተከፍሉ በመንደር ይቀርና የጌታውን ክብር እንዲጠብቅ ይደረጋል...” ብሏል ። በሌላው የመጽሐፉ ገጽ ላይ ደግሞ ባዶሊዮ ይህንኑ ጉዳይ አንስቶ “...በኢትዮጵያውያን ጦር መሪዎች መሀል መለያየትና የውስጥ መጠራጠር እንደተፈጠረው ሁሉ ወታደሩም ጌታውን እየተከተለ ተሽከክሯል ። ለዚህ ሁሉ መለያየት ያበቁት ንጉሡ ናቸው ።... ራስ ስዩም ፤ የግል ጉዳይ የሆነ የማዕረግ ነገር ቂም አለባቸው ። ራስ ካሣ ጥሩ የቤተ ክርስቲያን ሰው ናቸው ። ሙሉጌታ ጦረኛና በጦር ያደገ ሰው ነው ። በዚህም በጦረኛነቱ ምክንያት ጠቅላይ የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ ሆኖ ተሾሞ ነበር...” ብሏል ።

ባዶሊዮ ራስ ሙሉጌታን “... ተሾሞ ነበር...” ያለው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ጦር አዛዥ የነበሩት ራስ ሙሉጌታ ተሽረው ራስ ካሣ ከተሾሙ በኋላ ያተተው ነው ። ስለራስ ሙሉጌታ መሻርና ስለራስ ካሣ መሾም ባርከር ሲጽፍ “...ንጉሡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከታላላቅ ሰዎች የተወለዱ ናቸው እንጂ የጦር አመራር ችሎታ ያላቸው አይደሉም ። ለመጀመሪያ ጊዜ ጦርነቱ ውስጥ ለመግባት ደሴ ሲደርሱ የሥራ መጀመሪያ ያደረጉት ራስ ሙሉጌታን ሽረው የቅርብ ወዳጃቸውን ራስ ካሣን መሾም ነበር ። የጦር ሚኒስትሩ (ራስ ሙሉጌታ) የታወቀ ጉበዝ ሰው ነበር ። የሚጠበቀውና የሚፈራውም የሱ ጦር አመራር ነበር ። የወታደሮች ወታደር ነበር ። ራስ ካሣ ግን ምንም የጦር ጥበብ የማያውቅ ሰው ነው ። ከነገሥታት ትውልድና በፖለቲካም ተሰሚነት ስላለው ብቻ ጠቅላይ ጦር አዛዥ ሆነ ። ለዚህ ነው ባዶሊዮ የሙሉጌታን መሻርና የካሣን መሾም ሲሰማ የተደሰተው ።...” ካለ በኋላ በሌላ የመጽሐፉ ገጽ ደግሞ “... ሙሉጌታ ተሽሮ ካሣ ሲሾም አምባራዶም ያለው ሙሉጌታና ጉንደር ያለው እምሩ የካሣን ትእዛዝ ላለመስማት ጆሮአቸውን ደፈኑ ። ሙሉጌታ የሚደርሰውን ትእዛዝ እንዳልሰማ እየሆነ ምንም የሰማሁት የለም ይላል ። እምሩም የተነሳብኝን ያዥ ውስጥ ሽፍታ በመከላከል ላይ ነኝ እያለ አይታዘዝም ። የካሣ ትእዛዝ ተቀባይ አጣ ። እንዚህ ሁለት ታላላቅ ጦረኞች የሚያስቡት አሳብ ካሣ የሚገጥመውን ግጥም እንዲዋረድና ክፍ ያደረገው የንጉሡ ዓይን ዝቅ እንዲያደርገው ነው...” በማለት ይተነትናል ።


ባርከር “...የተፈራው ጦር የሙሉጌታ ነበር...” ያለው እውነቱን ነው ። ይህን ነገር የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ባዶሊዮም በመጽሐፉ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል “...የጦር ሚኒስትሩ ሽማግሌው ራስ ሙሉጌታ በአድዋ ዘመቻ ክንዱን ያሳየ በመሆኑ የኢትዮጵያን ጦር ፈርተን ብዙ መጣሪያ አከማችተን ነበር ። ጦርነቱ እንደተጀመረ ንጉሡ ፤ ራስ ሙሉጌታን ሽረው ቂሱን ራስ ካሣን የጦር ሚኒስትር አድርገው በመሾማቸው የኢጣሊያ ጦር በቀላሉ ድል እንደሚያደርግ ገብቶን ተደሰትን ። በመኳንንቱ መሐል ባለው የርስ በርስ ያለ መግባባትም ተጠቀምን ። ንጉሡም የራስ ሙሉጌታን ሠራዊት እንዲከዳ ስላደረጉ ራስ ሙሉጌታን ከጥቂት ከተረፉት ታማኝ ወታደሮቹ ጋር አዳል በረሃ ውስጥ አግኝተን በአይሮፕላን መትረየስ ገደልነው ። በዚህም በሙሉጌታ ሞት የኢትዮጵያውያንን ሞራል ሰበርነው...”

በኢትዮጵያውያን መሀል ባለው ያለመግባባትና መለያየት ምክንያት ከውጭ አገር ኢትዮጵያን ለመርዳት የተነሱና በኢጣሊያ ግፈኛነት የተበሳጩ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ተቀባይ አጡ ። ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ባወጀች ጊዜ ከእንግሊዝ አገር ብቻ ሶስት ሺ ሰዎች ኢትዮጵያን ለመርዳት በወዶ ዘማችነት ተመዝግበው ነበር ። እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 4 ቀን 1935 ዓም የወጣው ዴይሊ ኤክስፕሬስ ጋዜጣ “...ንጉሡ ይህን እርዳታ አልተቀበሉትም ። ያልተቀበሉበትም ዋናው ምክንያት ለእነዚህ ሰዎች የሚከፈል ነገር የለም ብለው ነው ። ከኢትዮጵያውያን ጉን ተሰልፈን እንዋጋለን ያሉት እንግሊዞች ብቻ ሳይሆኑ በራንግል አርሚ ውስጥ የነበሩና ከገራቸው የከዱ ሩሲያውያን ፤ ቱርኮች ፤ ሁንጋሪያውያኖችና ቼኮዝሎቫኪያን


ሁሉ ናቸው ።…” ብሏል ። ይህ ብቻ ሳይሆን በኒውዮርክ ከተማ ያሉ አሜሪካውያን በሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት የኢጣሊያን አድራጎት ተቃወሙ ። በማዲሰን አደባባይ የተሰበሰቡ ዘጠኝ ሺ አሜሪካውያን የሙሶሊኒን ፎቶግራፍ በማቃጠል ተቃውሞአ ቸውን ገለጡ ። በኢጣሊያ ውስጥም ቢሆን ሳይፈሩ አድራጎቱን የተቃወሙ ሰዎች ነበሩ ። በጀርመን ሲኒማ ቤቶችም የሙሶሊኒን ጦር ማጋዝና ማከማቸት የሚያሳየው “ኢትዮፒያ 1935” የተባለው ፊልም ለሕዝብ እየታየ ሕዝቡ ተቃውሞውን ይገ ልጽ ነበር ። በካይሮም የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች በየመስጊዱ ሕዝቡን እየ ሰበሰቡ ኢትዮጵያን በግፍ ከመጣባት መከራ እንዲያድናት እንዲፀለይ አዘዙ ።

ይህ ሁሉ ቢሆንም ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሪዎች ስህተትና በመሣሪያ እጥረት ድል እየሆነ ይሄድ ጀመር ። ባዶሊዮ ራሱ ሲመሰክር “… የኢጣሊያ አይሮፕላኖች ዘመናዊና ባለሙሉ ትጥቅ ባይሆኑ ኖሮ ኢትዮጵያውያን የአድዋውን ድል እንደገና ይደግሙ ነበር ። በፓይለቶቻችን ታላቅ ተግባር ኢጣሊያኖች ድል ለማድ ረግ በቃን ።…” ብሏል ። ይህንንም ወደፊት በየጦሩ ግንባር እናገኘዋለን ።

———O———



የክብር ዘበኛ ጦር



የክብር ዘበኛ ጦር